# የግብረ ገብ ትምህርት
## የተማሪ መፅሐፍ
## 2ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዪኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ
አስተዳደር ትምህርት
ቢሮ

የግብረ ገብ ትምህርት የተማሪ መፅሐፍ ሁለተኛ ክፍል

# የግብረ ገብ ትምህርት
## የተማሪ መፅሐፍ
## 2ኛ ክፍል



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ
ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዪኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ
አስተዳደር ትምህርት
ቢሮ

# ይህ መጽሐፍ በጥንቃቄ ይያዝ!



የመማሪያ መጽሐፍ የትምህርት ቤታችሁ ንብረት ነው።
ስለዚህም እንዳይጎዳ ወይም እንዳጠፋ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጉ።
መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ይረዷችሁ ዘንድ የሚከተሉትን 10 ነጥቦች አስተውሉ።

1. መጽሐፉን እንደ ፕላስቲክ፣ ጋዜጣ እና በመሳሰሉ ቁሶች መሸፈን፣
2. መጽሐፉን ንጹህ እና ደረቅ ቦታ ማስቀመጥ፣
3. መጽሐፉን በሚጠቀሙ ጊዜ እጅዎት ንጹህ መሆኑን ማረጋገጥ፣
4. በመጽሐፉ ሽፋንም ሆነ የውስጥ ገጾች ላይ አለመጻፍ፣.
5. ገጾችን ከማጠፍ ይልቅ ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድ ለምልክት መጠቀም፣
6. ማናቸውንም ምስሎች ወይም ገጾችን ፈጽሞ አለመቅደድ፣
7. ማናቸውንም የተቀደዱ ገጾች መጠገን፣
8. መጽሐፉን በቦርሳ ውስጥ በጥንቃቄ ማስቀመጥመጽሐፉን
9. ለሌላ ሰው ሲያውሱ በጥንቃቄ ማቀበል፣
10. አዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠቀሙ፤ መጽበጀርባ ሽፋኑ በኩል ማስቀመጥ ከዚያም በአንድ ጊዜ ውስን ገጾችን መግለጽ፤እንዲሁም የመጽሐፉን ጠርዞች በትንሹ ጫን ጫን ማድረግ። ይህም የመጽሐፉ ሽፋን በጥሩ ሁኔታ እንዲቆይ ይረዳል።

# የግብረ ገብ ትምህርት

# ሁለተኛ ክፍል

# የተማሪው መፅሐፍ


**አዘጋጅ** ተስፋዬ ጅማ (P.H.D)

ምናስ አዱኛ (Ass.Profesor)

**አርታዒዎች** አለማየሁ ነጋሽ (P.H.D)

ቃለወንጌል ምናስ (P.H.D)

ሙሉጌታ ያየህ (P.H.D)

**ሰዓሊ** ኤልዛልሞን ጌቱ(M.Sc)

**ሌይአዉት ዲዛይነር** አብርሃም ሰሎሞን (B.Sc)(አለማምት የሰራዉ)

ናትናኤል ዉብሸት (M.Sc)

**ተርጓሚዎች** ሀይሉ ተሸመ (M.A)

መስፍን አበበ (M.A)

**አርታኢና ገምጋሚ** ምህረቱ ዋሌ(M.A)

**አስተባባሪ** ጊታቸዉ ታለማ(M.A)



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ልዩ በሆኑ እሴቶቸ ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ቅርሶቸ በስፋት የምትታወቅ ሀገር ናት፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ እሴቶች ለዘመናት የተረጋጋችና ቀጣይነት ያላት ማህበረሰብ እና ሀገር እንድትሆን እንደ መሳሪያንት አገልግለዋል፡፡ በዚህም መሰረት እነዚህን እሴቶችና ባህሪያት በእንክብካቤ በመጠበቅ ለአዲሱ ትውልድ ተሸጋግረዋል፡፡

የግብረገብ ትምህርት እንደ ልዩና ወሳኝ ትምህርት በትምህርት ሥርአቱ መካተት ማህበረሰባችን የሚያከብራቸውን እሰቶችና ልማዶችን እንድናስተምርና እንድናስቀጥል ያስችለናል፡፡ ዘመናዊ የግብረገብ ትምህርት ጥሩና ትክክለኛ የማህበረሰቡን ባህሪያት ለቀጣይ ትውልድ የምናስተላልፍበት መንገድ ነው፡፡

እውነተኛዋ ኢትዮጵያ የብዝሀነት ፣ አካባቢያዊ ቋንቋ፣ ማህበረሰባዊና ባህላዊ ልዩነቶች ጎልቶ የሚታይባት አገር ናት፡፡ለዘመናት ጠብቀው የኖሩት ማህበራዊ ግንኙነትና ትስስሮች በጋራ ሊኖራቸው የሚችሉትን ግብረገባዊ እሴቶችን እንደ ማህበረሰብ እንዲያጎለብቱ ረድቷቸዋል፡፡ለምሳሌ ታላላቆችን ማክበር፣ ጥሩ ጉርብትና ፣ እንግዳ ተቀባይነት፣ ማህበራዊ ድጋፍና የመረዳዳት ባህሪያት በስፋ የሚተገበሩ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እነዚህ ግብረገባዊ ባህሪት በሀገሪቱ ወጣት ዜጎች ላይ የመቀነስ አዝማሚያ ይታያል፡፡ ስለዚህ የግብረገብ ትምህርት መስጠት እጅጉን አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት በግብረገብ የታነጸ ጥሩ ዜጋን ለማፍራት አላማ ሲባል በስርአተ ትምህርቱ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

የሁለተኛ ክፍል መርሀ ትምህርት በዋናነት የሚያተኩረው መልካም ማህበራዊና ግብረገባዊ እሴቶችን የመገንባት ሂደት ላይ ነው፡፡ የትምህርቱ ይዘት የተገነባው ባለፈው የትምህርት ደረጃ ከተሸፈነው በተጨማሪ አዲሱን በማስተዋወቅ ላይ ነው ፡፡ የትምህርቱ ጥልቅ አላማ ካለፈው ትምህርት በመነሳት አዳዲስ እሳቤዎችን በማስተዋወቅ ተማሪዎችን መደገፍና ባህሪያቸውን መገንባት ማስቀጠል ነው፡፡

የዚህ ክፍል ደረጃ የትምህርት ይዘት በዋናነት የሚያተኩረው ግለሰባዊ ባህሪያትን ተንተርሶ ከሌሎች ዜጎች ጋር አወንታዊ ግንኑነትን ማሳለጥ ላይ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምእራፍ ራስን ማክበር ላይ የሚያተኩርና የግለሰባዊ የግብረገብ ባህሪና የስነምባር እድገት መሰረት ነው፡፡ሌሎችን ማክበር የሚጀምረው ራስን በማክበር ነው፡፡በተጨማሪም የተማሪዎችን ባህሪ በሀቀኝነትና በታማኝት፣ ትክክለኛነትና ፍታሀዊነት፣ በጋራ ጥቅምና ተግባር ላይ በማተኮር አወነታዊና ማህበረሰባዊ ትስስር በመፍጠር ይመራል፡፡ የነዚህ ግብረገባዊ ባህሪያት በግለሰብ ደረጃ መገንባት በማሀበረሰብ ውስጥ መልካም ግንኑነትን በማሳለጥ አንድነትን ይፈጥራል፡፡የእነዚህ ግለሰባዊ ባህሪያት በውስጣዊነት ለአንድ ግለሰብ ጥሩ ሲሆኑ በውጫዊው ደግሞ ግብረገብነት ያለው፣ የበለጸገና ሰላማዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

# ማውጫ

ይዘቶች ገፅ


ምዕራፍ አንድ .......................................................................1

ራስን ማክበርና በደህንነት መቆየት...................................................1

1.1. ራስን ማክበር........................................................1

1.2. ራስን ማክበር አስፈላጊነት...............................................3

1.3. የራስን ክብር መገንቢያና ማሳያ መንገዶች...........................4

1.4. በደህንነት መቆየት..................................................9

1.5. ልጆችን በደህንነት እንዲቆዩ የሚረዱ መንገዶች..................9

ምዕራፍ ሁለት.................................................................... 16

እውነትን እና ታማኝነትን መሻት.............................................. 16

2.1. የእውነተኛነትና ታማኝነት ምንነት................................. 16

2.2. የእውነተኛነትና ታማኝነት አይነቶች............................... 17

2.3. የእውነተኛና የታማኝ ሰው መለያ ባህርያት.................. 19

2.4. የእውነተኝነትና የታማኝነት አስፈላጊነት........................ 20

2.5. እውነተኛና ታማኝ የመሆን አስፈላጊነት...........................22

2.6. የእውነተኛነትና ታማኝነት አለመኖር ጉዳቶች.................... 25

ምዕራፍ ሦስት...........................................................................30

ፍትህ................................................................................ 30

3.1. የፍትህ ምንነት.................................................... 30

3.2. የፍትህዊነት አስፈላጊነት......................................35

3.3. የፍትህዊ ሰው ባህሪያት.............................................36

3.4. የፍትህዊነት አለመኖር ውጤቶች.................................. 37

3.5. ኢፍታዊነትን መታገል............................................ 39

ምዕራፍ አራት....................................................................44

አወንታዊ ማኀበራዊ መስተጋብር................................................ 44

4.1. የአወንታዊ ማህበራዊ መስተጋብር ምንነት........................44

4.2. አወንታዊ ማኀበራዊ መስተጋብሮችን ማሳደጊያ መንገዶች............51

4.3. የአወንታዊ ማህበራዊ መስተጋብሮች አስፈላጊነት...............52

4.4. የአወንታዊ ማኀበራዊ መስተጋብር እንቅፋቶች...................53

ምዕራፍ አምስት................................................................ 58

ለጋራ ጥቅም መቆም ........................................................ 58

5.1. የጋራ ጥቅም ምንነት................................................... 58

5.2. ለጋራ ጥቅም ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነት....................60

5.3. ለሌላ ሰው በጎ ስራ መስራት............................................ 62

5.4. ግለኝነትና የጋራ ጥቅም................................................ 64

5.5. የጋራ ጥቅም ዋና ዋና ክፍሎች........................................ 65

5.6. የጋራ ጥቅም እንቅፋቶች................................................68

ምዕራፍ ስድስት................................................................. 71

ባህላዊ ቅርሶች....................................................................71

6.1. የባህላዊ ቅርስ ምንነት................................................. 71

6.2. የባህላዊ ቅርስ አይነቶች............................................... 73

6.3. የባህላዊ ቅርሶች የመጠበቂያ መንገዶች.........................78

6.4. የባህላዊ ቅርሶች አስፈላጊነት.........................................80

# ምዕራፍ አንድ

## ራስን ማክበርና በደህንነት መቆየት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የራስን ማክበር ፅንሰ ሀሳብ ትገልፃላችሁ
- ለራስ ማክበር ጥቅም ዋጋ ትሰጣላችሁ
- የራስ ማክበር መንገዶችን ትለያላችሁ
- ራስን ማክበር እንዴት መገንባት እንዳለበት ትገልጻላችሁ
- ራስን ከአካላዊና ስሜታዊ ጎጂ ልማዶች እንዴት መከላከል እንደሚቻል ትጠቁማላችሁ::

### 1.1. ራስን ማክበር

ውድ ተማሪዎች:- ራስን ማክበር ምን ማለት ነው? መልሱን ለመምህራችሁ ተናገሩ::

ራስን ማክበር ማለት በራስ መተማመን፣ ራስን ማሞገስ፣ በክብርና በስርዓት ማስኬድ ማለት ነው፤ እንዲሁም ለራሳችን የምንሰጠው ክብር ነው::



ምስል 1.1፡ በራሱ የሚኮራ ልጅ

ተግባር 1:- ከላይ ያለው ምስል ምንን ያመለክታል? ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ለክፍሉ ግለጹ::

### ለቤተሰብና ለጎረቤት እንክብካቤ ማድረግ

ሃና ኤጀርሳ ጎሮ በምትባል አነስተኛ መንደር ትኖራለች። ከእለታት አንድ ቀን ጨው፣ ቡናና ሽንኩርት ለእናቷ ለመግዛት ወደ ገበያ በምትሄድበት ወቅት ጎረቤታቸው እትዬ አባቦ ለእሳቸውም እንድትገዛላቸው ጠየቋት። እትዬ አባቦ የሃና እናት ጓደኛ ሲሆኑ የሚረዳቸው ልጅ የሌላቸው በመሆኑ ሃና ዘወትር እትዬ አባቦ የሚስፈልጋቸውን ድጋፍ በደስታ ትሰጣለች።



ምስል 1.2 እትዬ አባቦ የሃናን እናት ስያናግሩ እና ሃና ገበያ ስትገበያይ

**ተግባር 2፡- ከላይ ያለው ምስል ምን ያመለክታል?**

### የግለሰብን ልዩነቶችን ማድነቅና ማክበር

ዮናታንና ኤባ የትምህርት ቤት ጓደኞሞች እና የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ትምህርት ቤታቸው በወር አንድ ጊዜ ባህላዊ ክብረ በዓል ቀን ለተማሪዎች ያዘጋጃል። ስለዚህም ዮናታን እና ኤባ ለበዓሉ ያዘጋጅቱን መዝሙር ለማቅረብ ባህላዊ ልብሶቻቸውን ይለብሳሉ። በባህላዊ ክብረ በዓል ቀንም በትምህርት ቤታቸው ግቢ ውስጥ ሲገናኙ የጓደኞቻቸውን የባህላዊ አለባበስ ዘዴ፣ የልብሶቻቸውን ቀለም ወዘተ ያደንቃሉ።



ምስል 1.3 ተማሪዎች የግለሰብ ልዩነቶችን ሲያከብሩና ሲያደንቁ

ተግባር 3፡- ከላይ ያለው ምስል ምን ያመለክታል?

## 1.2.ራስን የማክበር አስፈላጊነት

ራስን ማክበር አስፈላጊ ነው ምክንያቱም በራሳችን እንድንተማመን፣ በሌሎች እንድንከበር፣ በኑሮአችን ውጤታማ እንድንሆንና ጽናትን እንድናዳብር ያስችለናል፡፡ በተጨማሪም ራስን ማክበር ስለ ቆምንለት ዓላማና እሴቶቻችን ማወቅን ያካትታል፡፡ እንዲሁም ድክመቶቻችንን እና ጥንካሬዎቻችንን አምነን መቀበል ማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክብር በመንታ መንገድ ይመሰላል፡፡ ይህም ማለት እናንተ ሌሎች የሚገባቸውን ክብር የማትሰጡ ከሆነ ምናልባት እራሳችሁን ልታከቡሩ ትችላላችሁ ነገር ግን ሌሎች ለእናንተ የሚገባችሁን ክብር ላይሰጧችሁ ይችላሉ፡፡

ተግባር 4፡- ከላይ በተሰጠው አንቀፅ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ተወያዩባቸው፡፡

1. ራሳችሁን በምን አይነት መንገድ ታከብራላችሁ?
2. ቤተሰባችሁን (አባትን፣ እናትን፣ ወንድምና እህትን) በምን አይነት መንገድ ታከብራላችሁ?
3. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታላላቆቻችሁን ምን ምን በማድረግ ታከብራላችሁ?
4. ራስን የማክበር ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?



ምስል 1.3 ራስንና ሌሎችን ማክበር

ተግባር 5፡- የላይኛው ምስል ምንን ያመለክታል?

## 1.3.የራስን ክብር መገንቢያና ማሳያ መንገዶች

የተለያዩ የራስ ክብር ማሳያ መንገዶች አሉ፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉት ምስሎችና ተግባሮች የራስ ክብር ልምዶችን ያሳያሉ፡፡

የትምህርት ቤት ደንቦችን መከተል

የሚከተሉት ህግና ደንቦች በክፍል ኃላፊ መምህር የተለጠፉ ናቸው፡፡

- ወደ ት/ቤት ስትሄዱ የደንብ ልብሳችሁን ልበሱ፡፡
- በክፍል ውስጥ መልስ በምትመልሱበት ጊዜ እጃችሁን አውጡ፡፡
- መምህራን ወደ ክፍል ሲገቡ ከመቀመጫችሁ ተነሱ፡፡



ምስል 1.4 የደንብ ልብስ በመልበስ የትምህርት ቤትን ደንብ ሲያከብሩ



ምስል 1.5 ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እጃቸውን በማንሳት መልስ በመመለስ የትምህርት ቤት ደንብን ሲያከብሩ



ምስል 1.6 ተማሪዎች የክፍል ሥራ በመስራት የትምህርት ቤት ደንብን ሲያከብሩ



ምስል 1.7 ተማሪዎች የመምህራቸውን መምጣት በክፍል ውስጥ በመጠበቅ የትምህርት ቤት ደንብን ሲያከብሩ



ምስል 1.8 ተማሪዎች ተነስተው መምህራቸውን በመቀበል የትምህርት ቤት ደንብን ሲያከብሩ

ተግባር 6፡- ከላይ የተቀመጡት ምስሎች ምንን ያመለክታሉ? በሰዎች መካከል የሚገኙ ልዩነቶችን ማድነቅና አንድ ሰው የሚጠላውን እና የሚወደውን ነገር ዋጋ መስጠት፡፡

## ማርያማዊት እና ፋጡማ

ማርያማዊትና ፋጡማ ጐረቤታሞችና የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሳምንቱ መጨረሻ ማርያማዊት ፋጡማን እና የፋጡማን ቤተሰቦች ወደ ወላጆቿ ቤት ምሣ እንዲበሉና ቡና አብረው እንዲጠጡ ትጋብዛቸዋለች፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ፋጡማም ማርያማዊት እና የማርያማዊትን ቤተሰቦች ወደ ወላጆቿ ቤት እራት እንዲበሉና ቡና አብረው እንዲጠጡ በሣምንቱ መጨረሻ ቀናት ትጋብዛቸዋለች፡፡



ምስል 1.9 ማርያማዊት ፋጡማንና የፋጡማን ቤተሰቦች በወላጆቿ ቤት ውስጥ እየጋበዘች



ምስል 1.10 ፋጡማ ማርያማዊትንና የማርያማዊትን ቤተሰቦች በወላጆቿ ቤት ውስጥ እየጋበዘች

## ልዩነቶችን ማድነቅ

ተግባር 7፡- ከላይ የተገለፁትን ምስሎች እና ትረካ መሰረት በማድረግ በቡድን ተወያዩባቸው፡፡

### አካባቢን መንከባከብ

ቤታችሁን ካልተንከባከባችሁ ራሳችሁን ልትንከባከቡ አትችሉም፡፡ የቤት ፅዳት የቤትን ውበት ይጨምራል፡፡ በተጨማሪም በሚያማምሩ ነገሮች መሙላት ማራኪና ውብ ቤት እንዲኖረን ይረዳናል፡፡ ይህ የሚያሳየው የራሳችሁን ቤት እንዴት እንደምትንከባከቡና መልካም ባህሪ እንዳላችሁ ነው፡፡



ምስል 1.11 ልጆች አካባቢያቸውን ሲንከባከቡ

ተግባር 8፡- የላይኛው ምስል ምንን ያመለክታል?

## 1.4.በደህንነት መቆየት

በደህንነት መቆየት ማለት ራስን ጎጂ ከሆኑ ነገሮችና ሁኔታዎች መጠበቅ ነው፡፡ ደህንነት ከአደጋ ነፃ መሆን ማለት ነው፡፡ በደህንነት መቆየት ራስን ከማንኛውም ጎጂ እና ጉዳት ማራቅ ማለት ነው፡፡ ደህና መሆን ማለት ደህንነት ማለት ነው፡፡ ካልተጠነቀቅን ብዙ ሊጎዱን የሚችሉ ነገሮች አሉ፡፡ በደህንነት በህይወት ለመቆየት በተቻለን አቅም ዘወትር የደህንነት ደንቦችን መከተል አለብን፡፡ በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት፣ በመንገድ ላይ ወዘተ የሚገኙ የደህንነት ደንቦችን መከተል ይኖርብናል፡፡

ተግባር 9፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያዩባቸው፡፡

1. በቤት ውስጥ እንዴት ደህንነታችሁ ተጠብቆ መቆየት ትችላላችሁ?
2. በትምህርት ቤት ደህንነታችሁን ለመጠበቅ ምን ታደርጋላችሁ?

## 1.5.ልጆችን በደህንነት እንዲቆዩ የሚረዱ መንገዶች

ልጆች በደህንነት እንዲቆዩ የሚረዱ ብዙ ዓይነት መንገዶች አሉ፡፡ የሚከተሉት ልጆች አደገኛ አካባቢዎች በሚሆኑበት ጊዜ ሊያስተውሏቸው የሚገቡ የደህንነት ልማዶችና ቅድመ ጥንቃቄዎች ናቸው፡፡

- እንስሳት በሚበሉበት፣ በሚተኙበት እና ከልጆቻቸው ጋር በሚሆኑበት ጊዜ አታባሯቸው ወይም አታስቸግሯቸው፡፡
- ብቻችሁን አትዋኙ፡፡
- መንገድ ሲጠፋባችሁ ሰው ወዲያውኑ ጠይቁ፡፡
- ብቻችሁን መንገድ አታቋርጡ፡፡
- መኪኖች ባሉበት ቦታ ላይ ያለ ፈቃድ መንገድ ላይ አትጫወቱ፡፡
- ስለታማ በሆኑ ነገሮች አትጫወቱ፡፡



ምስል 1.12 አባት ለልጆቹ የደህንነት ምክር ሲሰጥ



ምስል 1.13 ቤተሰቡ ጤናማ ምግቦችን ሲመገብ



ምስል 1.14 ልጆች ከእናትና አባታቸው ጋር ብስክሌት እየነዱ

ተግባር 10፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በላይኞቹ ምስሎች መሰረት በመመለስ በደብተራችሁ ላይ አስፍሩዋቸው፡፡

1. የላይኞቹ ምስሎች ምንን ያመለክታሉ?
2. ጥሩና ጤናማ ምግቦችን በምን አይነት መንገዶች ብንመገባቸው ደስተኛና ጤናማ እንሆናለን?
3. ከላይ የተቀመጡት ደንቦች ጤንነታችሁን እና ደህንነታችሁን እንዴት ለመጠበቅ ይረዷችኋል?

## በሽታን መከላከል እና ደህንነትን መጠበቅ

ራሳችሁን ከበሽታ ለመከላከል እና በደህንነት ለመቆየት የሚከተሉትን ቅደመ ጥንቃቄዎች ማድረግ አለባቸችሁ፡-

- ✓ መፀዳጃ ቤት ከተጠቀማችሁ በኋላ፣ አፍንጫችሁን ካፀዳችሁ በኋላ እንዲሁም ምግብ ከመመገባችሁ በፊት እጃችሁን በደንብ መታጠብ፡፡
- ✓ ኮፍያ፣ የፀጉር ማበጠሪያ፣ የጥርስ ቡርሽ ወይንም የግል መጠቀሚያ ነገሮችን ለሌሎች አታውሱ፡፡
- ✓ በሚያስነጥሳችሁ ወይም በሚያስላችሁ ጊዜ አፋችሁን በእጃችሁ ሸፍኑ፡፡
- ✓ የሌሎች ልጆችን ደም፣ ሽንት፣ አይነ ምድር /ሰገራ/ ወይንም ማንኛውንም ከሰውነት የሚወጣ ፈሳሽ አለመንካት፡፡

ተግባር 11. ከዚህ በታች ካለው ምስል ምን ትማራላችሁ?



ምስል 1.14 ከጨዋታ በኋላ ልጆች እጃቸውን ሲታጠቡ



ምስል 1.15 ልጆች ምግባቸውን በራሳቸው ማንኪያ ሲመገቡ



ምስል 1.16 ልጆች በሚያስነጥሳቸው ጊዜ አፋችሁን ሲሸፍኑ

**ተግባር 12፡- ከሚከተሉት ድርጊቶች ውስጥ የትኞቹ በደህንነት ያለና በደህንነት የሌለ ልጅን ያሳያሉ?**

1. ለብቻ መዋኘት
2. የሌሎች ልጆችን ደም እና ሽንት መንካት
3. በስለታማ ነገሮች አለመጫወት
4. የሌሎችን ኮፍያ ፀጉር ማበጠሪያና ማንኪያ መጋራት
5. መኪናዎች በሚገኙበት ቦታ መጫወትና መንገድን ለብቻ ማቋረጥ
6. እጅን ከመፀዳጃ ቤት መልስ አለመታጠብ
7. በግልፅ ከወላጆት ጋር አለማውራት
8. እንስሳትን አለማባረርና ወይም አለማስቸገር
9. የወላጆችን የስልክ ቁጥር አለማወቅ

**የምዕራፉ ማጠቃለያ**

በዚህ ምዕራፍ ስለ ራስን ማክበር፣ የራስን ማክበር አስፈላጊነት፣ የራስን ማክበር ማሳያ መንገዶች፣ ልጆች ራሳቸውን እንዲረዱ የሚያግዙትን ራስን ማክበርን፣ መገንባትንና በደህንነት መቆየትን፣ ራስን ማወቅንና ሌሎችን ማክበርን ተምራችኋል። ይህ ማለት ራሳቸውን የሚያውቁ ልጆች በቀላሉ በአካባቢያቸው ያሉ ታላላቆችን፣ የሌሎችን ልዩነቶች ማክበርና ማድነቅ ይችላሉ። በተጨማሪም ልጆች ከማንኛውም አደጋ በደህንነት መቆየት ይኖርባችኋል። ስለዚህም ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤትና ማህበረሰቡ ልጆችን ከማንኛውም አደጋ ደህንነታቸውን የመጠበቂያ መንገዶችን ሊያስተምሩ ይገባል። እንዲሁም ልጆችም ቤተሰቦቻችሁንና አስተማሪዎቻችሁን በማዳመጥ የተማራችሁትን ደንብ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ይኖርባችኋል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አንብባችሁ ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ::

1. ለቤተሰብና ለማህበረሰብ እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም::
2. የግለሰቦችን ልዩነት ማክበር ሰላማዊ ኑሮን እንድንኖር ያግዘናል::
3. ራስን ማክበር በራስ መተማመንን አይሰጠንም::
4. መጸዳጃ ቤት በተጠቀማችሁ ቁጥር እጃችሁን መታጠብ ይኖርባችኋል::

በሚከተለው ሳጥን ውስጥ ደህንነታቸው የተጠበቀና ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ልጆች ባህሪያትን ጻፉ::

| ደህንነታቸው የተጠበቀ ልጆች መለያ ባህሪያት | ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ልጆች መለያ ባህሪያት |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

ከሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት አንዱ የጥሩ ስብዕና ግንባታ መገለጫ መንገድ አይደለም?
   - ሀ. የትምህርት ቤትን ደንብ መከተልና ማክበር
   - ለ. ልዩነቶችን ማድነቅ
   - ሐ. አንድ ሰው ለወደደውና ለጠላው ነገር ዋጋ መስጠት
   - መ. በክፍል ሀላፊ መምህር የሚለጡፉትን የክፍል ድንቦችን አለማክበር
2. ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ያስደስታችኋል?
   - ሀ. ራስን ማክበር
   - ሐ. በደህንነት መቆየት
   - ለ. ሌሎችን ማክበር
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸው
3. ከሚከተሉት ውስጥ ክብር የማይገባው የትኛው ነው?
   - ሀ. አንጋፋ ሰዎች
   - ሐ. ታናሽ ወንድም
   - ለ. ትክክለኛ ያልሆነ ሰው
   - መ. የቅርብ ጓደኛ
4. ከሚከተሉት ውስጥ በደህንነት እንድንቆይ የሚረዳን የትኛው ነው?
   - ሀ. መተላለፊያ መስመሮችን ማወቅ
   - ለ. ለብቻ መንገድ አለማቋረጥ
   - ሐ. ከወላጆች ጋር ስለደህንነት ማውራት
   - መ. ሁሉም መልስ ናቸው
5. ከሚከተሉት ውስጥ ደህንነታቸው የተጠበቀ ልጆች ባህሪያትን የሚያሳየው የትኛው ነው?
   - ሀ. ከመዳኛ ቤት መልስ እጅን ያለመታጠብ
   - ለ. የተጠቀሙበትን ማንኪያ ለሌሎች ማጋራት
   - ሐ. ስለታም በሆኑ ነገሮች ያለመጫወት
   - መ. የልጆችን ደም መንካት

# ምዕራፍ ሁለት

## እውነትን እና ታማኝነትን መሻት

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የእውነትና የታማኝነትን ምንነት ትረዳላችሁ
- የእውነተኝነትንና የታማኝነትን አይነት ትገልጻላችሁ
- የእውነተኛና የታማኝ ሰው መገለጫ ባህሪያትን ትለያላችሁ
- የእውነተኝነትንና የታማኝነትን ጥቅም ዋጋ ትሰጣላችሁ
- የእውነተኛና የታማኝ ሰው መገለጫ ባህሪያትን ታሳያላችሁ
- እውነተኛነትና ታማኝነት አለመኖር ውጤትን ትለያላችሁ።

## 2.1.የእውነተኛነትና ታማኝነት ምንነት

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን በመወያየት የደረሳችሁበትን መልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።

1. ለወላጆቻችሁ ለምን እውነት ትናገራላችሁ?
2. ለመምህራኖቻችሁ ታማኝ መሆን ለምን ያስፈልጋችኋል?

እውነት የሚለው ቃል የእምነት ማረጋገጫ፣ ከማስረጃዎቻች ጋር የሚዛመድ የተረጋገጠና ከሃቅ ጋር የሚዛመድ አረፍተ ነገር ነው። በሌላ አነጋገር አውነት ማለት የሆነውን የሆነበትን ምክንያት፣ ያልሆነውን ደግሞ ያልሆነበትን ምክንያት መናገር መቻል ማለት ነው።

የሀቀኝነት ጥሩ ጎን እውነተኝነት ይባላል፡፡ ትክክለኛነትና ታማኝነት የእውነት ቁልፍ አካላት ናቸው፡፡

ሀቀኝነት ማለት አንድ ነገር ምን ያህል እውነት እንደሆነና እንደተከሰተ መግለፅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ታማኝነት ማለት እውነት ብቻና ግብረገባዊ ትክክለኛነት ያላቸውን ነገሮች መናገር ወይም መስራት ማለት ነው፡፡ ታማኝነት እውነት መናገርን ወይም አለመዋሸትን ያካትታል፡፡ እንዲሁም በሀቀኝነት ነገሮችን መከወን፣ ግብረገባዊና ትክክለኛ ነገሮችን መስራትን ያጠቃልላል (ለምሳሌ አለመስረቅ ወይንም አለማጭበርበር)፡፡

## 2.2.የእውነተኛነትና ታማኝነት አይነቶች

ተማሪዎች የተለያዩ የታማኝነትና የእውነተኝነት አይነቶች እንዳሉ መረዳት አለባችሁ፡፡ ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 2.2.1. እውነትን መናገር

ስለ ታማኝነት ስታስቡ ‹‹አትዋሹ›› የሚለውን ግብረገባዊ ምክር አስታውሱ፡፡ ታማኝ መሆን ማለት እውነተኛ የሆኑ ነገሮችን መናገርና ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ እውነት ያልሆነ ነገር መናገር የመታመን ባህሪ አይደለም፡፡

ተግባር 1፡- ከሚከተሉት ድርጊቶች የትኞቹ እውነት መናገርን ያሳያሉ? ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩና መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

1. አንተ/ቺ በቤታችሁ ውስጥ ያለን ጠረጴዛ ሰበርክ/ሽ እንበል፡፡ እናትህ/ሽ ጠረጴዛውን ማን እንደሰበረው ስትጠይቅህ/ሽ ለእናትህ/ ሽ ስትመልስ/ሽ_______________

ሀ.ጠረጴዛውን እንደሰበርክ/ ሽ ተናግረህ/ሽ ይቅርታ ትጠይቃታለህ/ሽ፡፡

ለ. ጠረጴዛውን ማን እንደሰበረው እንደማታውቅ/ቂ ትነግራታለህ/ሽ፡፡

2. አንተ/ቺ እነ ዮርዳኖስ ቤት ሄደህ/ሽ እንድትጫወት/ቺ ተፈቅዶልሀል/ሻል እንበል።አንተ/ቺ ግን አልሄድክም/ሽም በዛ ፋንታ እነ ጉርሙ ቤት ተጫውተሀል/ሻል።ይሁን እንጂ አባትህ/ሽ ዛሬ እነማን ቤት እንደተጫወትክ/ሽ ሲጠይቅህ/ሽ ከሚከተሉት መልሶች የትኛውን ትሰጠዋለህ/ሽ?

ሀ. እነ ዮርዳኖስ ቤት እንደተጫወትክ/ሽ ትነግረዋልህ/ትነግሪዋለሽ።

ለ. እነ ጉርሙ ቤት እንደተጫወትክ/ሽ ትነግረዋለህ/ትነግሪዋለሽ።

ሐ. እነ ዮርዳኖስና እነ ጉርሙ ቤት እንደተጫወትክ/ሽ ትነግረዋለህ/ትነግሪዋለሽ

### 2.2.2. ቃልን መጠበቅ

መምህር ከበደ የሁለተኛ ክፍል የክፍል ሐላፊ መምህር ነው። እናም ከ1-3 ደረጃ ለሚወጡ ተማሪዎች በሰሚስተሩ መጨረሻ እስክሪብቶና ደብተር እንደሚሸልማቸው ቃል ገባላቸው። በመጨረሻም መምህር ከበደ ቃሉን ጠብቆ ለሶስቱ ተማሪዎች በሴሚሰተሩ መጨረሻ ሸለማቸው።

ተግባር 2፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩና የምታገኙትን መልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ።

1. ከመምህር ከበደ ምን ተማራችሁ?

2. መምህር ከበደ ቃሉን እንደጠበቀ ሁሉ እናንተም ቃላችሁን የምትጠብቁ ይመስላችኋል? ለምን?

### 2.2.3. አትስረቁ፤ አታጭበርብሩ

እውነትን ስትደብቁ ችግር ውስጥ እንደምትገቡ ማወቅ አለባችሁ። ምክንያቱም ድርጊታችሁ ግብረገብን መጣስ በመሆኑ እንደ ማታለልና ማጭበርበር ድርጊት ይወሰዳል።

ተግባር 3፦ ከሚከተሉት ድርጊቶች ውስጥ የትኛው ማታለልን ወይም መስረቅን ያመለክታል? ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት የምታገኙትን መልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ

1. እናትህ/ሽ ኮምፒውተር ላይ ለ 30 ደቂቃ ብቻ እንድትጫወት ፈቀደችልህ/ሽ እንበል። መቁጠሪያ ሰአትም አስቀምጣልህለች/አስቀምጣልሽለች፡ በመቀጠል የትኛውን ነገር ልታደርግ/ጊ ትችላለህ/ያለሽ?

ሀ. ሠዓቱ ሊያልቅ ሲል በድብቅ ተጨማሪ ሠዓት በሠአቱ ላይ እሞላና በኮምፒውተሩ ጨዋታዬን እቀጥላለሁ።

ለ. ሰአቱ ሲደውል የኮምፒውተር ጨዋታዬን አቆማለሁ።

2. አባትህ/ሽ 10 ብር ሰጥቶህ/ሽ ሙዝ እንድትገዛ/ዢ ፈቅድልህ/ሽ እንበል፡፡ አንተ/ቺ ግን በ5 ብር ብትገዛ/ዢ አባትህ/ሽ ስለገንዘቡ ቢጠይቅህ/ሽ ምን ትመልሳለህ/ሻለሽ?

ሀ. ሙዙን በ 7 ብር እንደገዛሁት እነግረዋለሁ።

ለ. ሙዙን በ 5 ብር እንደገዛሁት እነግረዋለሁ።

## 2.3 የእውነተኛና የታማኝ ሰው መለያ ባህርያት

### ዮናታን ሁል ጊዜ እውነት ይናገራል

ዮናታን ሁልጊዜ እውነት ይናገራል። ምክንያቱም ታማኝነት ከማንኛውም ነገር የበለጠ ጠቃሚ ነው ብሎ ያምናል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ልጆች ዮናታንን አሳባቂ ብለው ይጠሩታል።

ምክንያቱም እሱ ባለበት መጥፎ ነገር አድርገው እንደማያመልጡ ያውቃሉ። ዮናታን አጥብቆ እውነት መናገር መጥፎ ነገር ከሚያደርጉ ልጆች ጓደኝነት በእጅጉ ይበልጣል ብሎ ያምናል።

ተግባር 4፡- ከላይ በተሰጠው ጽሑፍ መሰረት ከዚህ በታች በተሰጡት ሁኔታዎች ዮናታን ምን ሊያደርግ እንደሚችል ወስኑና መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

1. አንድ ልጅ የዮናታንን እስክሪብቶ በጉልበት ወስዶ እስክሪብቶውን እንደወሰደበት ለሌላ ሰው ቢናገር ሊጎዳው እንደሚችል አስፈራራው።

ዮናታን____________________________________

2. ጎርቫቾ የተባለ የዮናታን የቅርብ ጓደኛ ከትምህርት ቤቱ ቤተመጽሐፍት መጽሐፍ ሰረቀ። ነገር ግን ጎርቫቾ ባደረገው ነገር ተጸጽቶ መጽሐፉን ለትምህርት ቤቱ ቤተመጽሐፍት ከመለሰ በኋላ በቤተመጽሐፍቱ ውስጥ ምን እንዳደረገ ለማንም እንዳይናገር ዮናታንን ጠየቀው።

ዮናታን____________________________________

3. ዮናታን በብዙ ሰዎች ዘንድ አድናቆት ያገኘውን አዲስ ፊልም እንዳያይ ወላጆቹ ስለከለከሉት ቅር ብሎታል። ነገርግን ኪሩቤል የተባለ የዮናታን ጓደኛ ስለፊልሙ አጨራረስ ጠየቀው።

ዮናታን____________________________________

## 2.4.የእውነተኝነትና የታማኝነት አስፈላጊነት

ታማኝነት ስለምንናገረውና ስለምናደርገው ነገር ትክክለኛ መሆኑን ይገልፃል። በተጨባጭ በምናደርጋቸው ግንኙነቶችና ተግባራትም ይገለፃል። ታማኝነት በእውነት ላይ ተመርኩዞ በትክክል የተደረገውን ክስተት መናገርን ያካትታል።

### ሐና

ሐና ከዩኒቨርሲቲ ተመርቃለች፣ በፍፁም አትዋሽም፣ ልትታመን የምትችል ሰው ናት። በዚህ ዘመን ስራ ቀጣሪዎች ታማኝ የሆነ ሰው እንዲሰራላቸው መፈለጋቸው እውነት ነው። ሐና በአንድ ኩባንያ ውስጥ ስራ ተቀጠረች ምክንያቱም ታማኝ ናት። በተጨማሪም በኩባንያው ውስጥ በፍጥነት የደረጃ እድገት አገኘች። ይህም የሆነበት ምክንያት ለስራዋ ፣ለቀጣሪዎቿና ለደንበኞቿ ታማኝ ስለሆነች ሲሆን ብዙ ጓደኞችንም አፍርታለች።

ተግባር 5፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በተሰጠው ትረካ መሰረት መልሱ። መልሳችሁንም በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

1. ሐና ታማኝ ልጅ ነች? ለምን?
2. ሐና ለምን ጥሩ ስራ አገኘች?
3. ሐና ብዙ ጓደኞች አሏት? ለምን?
4. እንደ ሐና መሆን ትፈልጋላችሁ? ለምን?
5. እንደ ሐና ታማኝ መሆን ለምን በጣም አስፈላጊ ሆነ?

ተማሪዎች, ታማኝ መሆን ለናንተ፣ ለመምህራኖቻችሁ እና ለወላጆቻችሁ ጠቃሚ መሆኑን ሁልጊዜ አስታውሱ።

ለወላጆቻችሁና ለመምህራኖቻችሁ ታምኝ ስትሆኑ ይወዷችኋል፣ ያምኗችኋልም። እርግጥ ነው ወላጆቻችሁና መምህራኖቻችሁ ወደፊት በአካልም ሆነ በአእምሮ በምትጎለምሱበት ጊዜ ከእናንተ ጋር በመሆን ሊከታተሏችሁ አይችሉም። ነገርግን እናንተ ሁል ጊዜ ለወላጆቻችሁና ለመምሁራኖቻችሁ ታማኝከሆናችሁበተዘዋዋሪእራሳችሁንእንደምትጠብቁና የግል ኑሮአችሁን መኖር እንደምትችሉ ታረጋግጡላቸዋላችሁ። ይህንን ፅንሰ ሀሳብ በአእምሮአችሁ ያዙና የሚከተለውን ተግባር መሰረት አድርጋችሁ ያላችሁን ሀሳብ ተለዋወጡ።

ተግባር 6:- የሚከተሉት ጥያቄዎች እምነትን ለማሳደር ከታማኝነት ጠቀሜታ ጋር ይዛመዳሉ። በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ።

1. ትምህርት ቤት ነህ/ሽ እንበል። አስተማሪህን/ሽ በእረፍት ጊዜ ወደ መጸዳጃ ለመሄድ ፈቃድ ጠየክ/ሽ። መምህሩም/ሯም እንድትሄድ/ጂ ፈቀደልህ/ችልሽ። ይሁንና አንተ/ች ወደ መጸዳጃ መሄድህን/ሽን ትተህ/ሽ እግርኳስ ሜዳ ላይ ፈቃድ የሰጠህ/ሽ መምህር ጋር እግርኳስ ሜዳ ቢያገኝህ/ሽ?

2. እግርኳስ እየተጫወትክ/ሽ ነው እንበል። በቤታችሁ የአትክልት ቦታ ያለውን የአበባ ማስቀመጫ ሰበርክ/ሽ። እንዳጋጣሚ ስትሰብር/ሪ እናትህ/ሽ አይታለች። እናትህም/ሽም አበባ ማስቀመጫውን ማነው የሰበረው ብላ ጠየቀችህ/ሽ። ነገር ግን አንተ/ች ማን እንደሰበረው እንደማታውቅ/ቂ መለስክላት/ሽላት።

## 2.5.እውነተኛና ታማኝ የመሆን አስፈላጊነት

እውነት ነው ታማኝ የሆኑ ተማሪዎች ይሸለማሉ፣ ተቀባይነት ያገኛሉ፣ በተጨማሪም በወላጆቻቸው፣ በጓደኞቻቸው እና በማህበረሰቡ አባላት ይደነቃሉ። ስለዚህ ታማኝነት የላቀ ትህትና መርህ ነው ሊባል ይችላል። ይህ ማለት ተማሪዎች ሁል ጊዜ ታማኝ መሆን አለባችሁ ማለት ነው።

## የታማኙ ሰው አጭር ትረካ



ምስል 2.1 ወንዝ በሚያቋረጥበት ጊዜ መጥረቢያው ከእጁ አምልጦ ውሀ ውስጥ ሲገባ



ምስል 2.2 ባለመጥረቢያው በአካባቢው የነበበረውን ዋናተኛ መጥረቢያውን በመፈለግ እንዲረዳው ሲማፀን

ታማኝነት

ከእለታት አንድቀን አንድ በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ የሚኖር ከበደ የሚባል ሰው ነበረ። ምንም እንኳን ደሀ ቢሆንም እውነተኛና ታማኝ ነበር። ከበደ በሰፈሩ ዳርቻ በምትገኝ አንዲት ትንሽ ጎጆ ውስጥ ይኖራል። ከበደ ወደ እርሻ ቦታ  የሚሄደው የአዋሽን ወንዝ አቋርጦ ነው።

አንድ ቀን ግን ወንዙን ሲያቋርጥ ድንገት መጥረቢያው ከእጁ አምልጦ ወንዙ ውስጥ ወደቀበት በዚህም በጣም አዘነ። በመቀጠልም በወንዙ አካባቢ የሚገኘውን ዋናተኛ መጥረቢያውን በመፈለግ እንዲረዳው ተማጸነው። ዋናተኛውም ተማጽኖውን ተቀብሎ እጁን ወደ ወንዙ ውስጥ አስገብቶ ከብር የተሰራ መጥረቢያ አወጣና ይሄ ነው ያንተ መጥረቢያ ብሎ ጠየቀው።

ከበደም እሱ የኔ መጥረብያ አይደለም ብሎ ለዋናተኛው መለሰለት። ምክንያቱም ከበደ የሚፈልገው የራሱን ከብረት የተሰራ መጥረቢያ ነበር። እንደገና ዋናተኛው እጁን ወደ ወንዙ አስገብቶ ከወርቅ የተሰራ መጥረቢያ አወጣና ከበደን መጥረቢያህን ውሰድ አለው። አሁንም ከበደ ለዋናተኛው ከወርቅ የተሰራው መጥረቢያ የሱ እንዳልሆነ ነግሮት አልወስድም አለው።

በስተመጨረሻም ዋናተኛው ከብረት የተሰራ መጥረቢያ አውጥቶ ፈገግ ብሎ ለከበደ ሰጠው። ከበደም ከሚገባው በላይ ተደስቶ ዋናተኛውን የራሱን ከብረት የተሰራውን መጥረቢያ ስላገኘለት አመሰገነው። ዋናተኛውም በከበደ ታማኝነት በጣም ተደንቆ ከብርና ከወርቅ የተሰሩትን መጥረቢያዎችን ለከበደ ስለታማኝነቱ ሸለመው። ከበደም በድጋሚ ተደስቶ ዘለለ። በመጨረሻም ዋናተኛውን ከልቡ አመሰገነው።

ተግበር 7፦- ከላይ በተሰጠው አጭር ትረካ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ መልሳችሁንም በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

1. ከበደ ታማኝ ሰው ነው? ለምን?
2. ዋናተኛው ለከበደ ምን ሸለመው?
3. ከበደ የብርና የወርቅ መጥረቢያዎቹን ለምን አልወስድም አለ?
4. ዋናተኛው ለከበደ ለምን ፈገግታ አሳየው?
5. ከበደ ለምንድነው ከሚገባው በላይ ተደስቶ ዋናተኛውን ያመሰገነው?
6. አንተ/ቺ ከበደን ብትሆን/ኚ እሱ ያደረገውን ታደርጋለህ/ሽ? ለምን?

## 2.6.የእውነተኛነትና ታማኝነት አለመኖር ጉዳቶች

### ቀበሮ ና የበጎች እረኛ

ይህን ሰው አትሁን!

ከእለታት አንድ ቀን ሀይሉ የሚባል የበጎች እረኛ ነበር፡፡ ስልችቶት ስለነበር የቀልድ ጨዋታ ለመጫወት ወስኖ ‘ቀበሮ መጣ፤ እባካችሁ እርዱኝ’ በማለት ጮኸ፡፡ ወዲያውኑ ጩኸቱን የሰሙ የሰፈሩ ሰዎች ዱላቸውን ይዘው ቀበሮውን ሊያባርሩና ሀይሉንም ለማዳን እየሮጡ ሲደርሱ ቀበሮው የለም፡፡ በንዴት ‘የታለ ቀበሮው’ ብለው ሲጠይቁት የበጎቹ እረኛ ሳቀባቸውና ሁላችሁንም አሞኘኋችሁ እዚህ ቀበሮ የለም አላቸው፡፡ ከዚያም የሰፈሩ ሰዎች በነገሩ ተበሳጭተው እረኛውን ጥለውት ሔዱ፡፡ ይሁን እንጂ የሰፈሩ ሰዎች ሁለተኛ እንዳያታልላቸው ቢያስጠነቅቁትም ከስህተቱ መማር ባለመቻሉ በተደጋጋሚ በተመሳሳይ ሁኔታ የሰፈሩ ሰዎችን አሞኛቸው፡፡ አንድ ቀን ሀይሉ እየጠበቀ ወዳለበት የበጎች መንጋ መስክ ቀበሮ ገባ፡፡ ከዚያም በጎቹን አንድ በአንድ መግደል ጀመረ፡፡ የበጎቹ እረኛም ድምፁን ከፍ አድርጎ ከዚህ በፊት እንደሚያደርገው ‘ቀበሮ!’ እባካችሁ እርዱኝ ብሎ ጮኸ፡፡

የሰፈሩ ነዋሪዎችም ጩኸቱን ቢሰሙም የተለመደ ቀልዱን እየተጫወተ ነው በማለት ሊረዱት ከቤታቸው ሳይወጡ ቀሩ፡፡ ሀይሉም ማንም ሊረዳው እንዳልመጣ ባወቀ ጊዜ ወደ ሰፈሩ ሮጠና ቀበሮው በጎቹ ላይ ጉዳት እንዳደረሰ አሰረዳቸው፡፡ የሰፈሩም ሰዎችም ሀይሉን ተከትለው ወደ በጎቹ መስክ ቢመጡም ቀበሮው በጎቹን ገሎ ጨርሷቸዋል፡፡ ሀይሉም እያለቀሰና እምባውን እየጠረገ “እርዱኝ ብዬ ስጣራ አንድም ሰው ሊረዳኝ ያልመጣው ለምንድነው ነው? ብሎ ጠየቃቸው፡፡ ይህንንም የሰሙ አንድ አዋቂና በነዋሪዎቹ የተከበሩ ሽማግሌ እንዲህ ብለው መከሩት፡- እኛ በእውነት በበጎቹ ላይ ስለተፈጸመው ነገር በጣም አዝነናል፣ ነገርግን ማወቅ ያለብህ እውነት እንኳን ቢናገር ውሸታም ሰውን ማንም አያምነውም፡፡

ተግባር 8፡- ከላይ በተሰጠው ትረካ መሰረት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይታችሁ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

1. ከላይ ከቀረበው ትረካ ምን ተማራችሁ?
2. እረኛው ከሰፈሩ ሰዎች እርዳታ ያላገኘው ለምንድነው?
3. እረኛው ታማኝ ሰው ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?
4. የሰፈሩ አዋቂና በነዋሪው ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሽማግሌ ለእረኛው ከተናገሩት ምን ተማራችሁ?
5. በእናንተ አስተሳሰብ ያለመታመን ውጤቶች ምንድን ናቸው?

### የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለእውነተኛነት፣ ታማኝነት፣ የእውነተኝነትና የታማኝንት አይነቶች፣ ስለ መለያ ባህሪያቶቻቸው፣ አስፈላጊነታቸው፣ የሚያጎናጽፋትን ክብር እና እውነተኛና ታማኝ አለመሆን የሚያስከትለውን ውጤት አይተናል፡፡ ይህም የሚያሳየው እውነተኛና ታማኝ ሰው በሌሎች ሰዎች ዘንድ ሁሌም ይታመናል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ውሸት የሚናገርና የማይታመን ሰው በሌሎች ሰዎች ዘንድ አይታመንም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የማይታመኑና እውነተኛ ያልሆኑ ሰዎች ተፈላጊነታቸው ይቀንሳል፡፡ በመጨረሻም የማይገባ ተግባራቸው የማህበረሰባቸውንና የራሳቸውን ስነምግባርና ግብረገባዊነት ይሸረሽራል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. ከዚህ በታች የተሰጡ ዐረፍተ ነገሮችን በማንበብ ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ሀሰት በማለት መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

1. ልትስተናገድበት በምትፈልገው መንገድ ሰዎችን ማስተናገድ አለብህ፡፡
2. የሰዎችን ሀሳብ ለማድመጥ እራስን ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
3. ለሰራኸው ስህተት ሌሎችን ተጠያቂ ማድረግ አለብህ/ሽ፡፡
4. ታማኝነት ማለት እውነተኛ መሆንና እውነትን አለመደበቅ ነው፡፡
5. አለመዋሸት ታማኝነትን ያመለክታል፡፡

II. ከዚህ በታች ለተቀመጡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ የሚዛናዊ ሰው ባህሪ የሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ. እሱ/ሷ ምክንያታዊ ነው/ች
   - ለ. እሱ/ሷ ደንብን ያከብራል/ታከብራለች
   - ሐ. እሱ/እሷ ለሌሎች ጥሩ ነገር ያደርጋል/ታደርጋለች
   - መ. ሁሉም
2. ታማኝነት የሚያካትተው የትኛውን ነው?
   - ሀ. እውነት መናገር
   - ለ. ግብረገባዊ የሆኑ ነገሮችን ብቻ ማከናወን
   - ሐ. አለመስረቅ ወይም ያለማጭበርበር
   - መ. ሁሉም

3. ታማኝነትና እውነተኛነትን የማይገልጸው የትኛው ነው?

ሀ. እውነት መናገር

ለ. ቃልን መጠበቅ

ሐ. ማጭበርበር

መ. አለመስረቅ

4. ታማኝ መሆን ያለብን ለማን ነው?

ሀ. ለቤተሰብ

ለ. ለመምህር

ሐ. ለጓደኛ

መ. ለሁሉም

5. ከሚከተሉት ውስጥ ያለመታመንና እውነተኛ ያለመሆን ውጤት የቱ ነው?

ሀ. ወላጆችህ/ሽ ላያምኑህ/ሽ ይችላሉ

ለ. ጓደኞችህ/ሽ ካንተ/ችጋር ያላቸውን ግንኙነት ያቋርጣሉ

ሐ. በመምህራኖችህ/ሽ ትገለላለህ/ሽ

መ. ሁሉም

# ምዕራፍ ሦስት

## ፍትህ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የፍትሀዊነትና ያለማዳላትን ምንነት ትረዳላችሁ::
- ለፍትሀዊነት ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣላችሁ::
- ፍትሀዊ አስተሳሰብ ያለውን ሰው አስተሳሰብ ታሳያላችሁ::
- ኢፍትሀዊነትና አድሎነት በትምህርት ቤት ብሎም በማህበረሰቡ ውስጥ ሲያጋጥማችሁ በተቃርኖ መቆምን ትገልጻላችሁ::
- የፍትህ አለመኖር የሚያስከትለውን ውጤት ትለያላችሁ::

### 3.1.የፍትህ ምንነት

ተማሪዎች ስለፍትህ ምን ታስባላችሁ? መልሱን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ:: ፍትህ ማለት ማንኛውንም ሰው ያለአድሎ በእኩልነት ማየት ነው:: ፍትህ ተጓድሎ ስናይ ወይም ሲከሰት ከተጎጂዎቹ ጎን በመቆም አጋርነታችንና ድምጻችንን በማሰማት መግለጽ አለብን:: በተለያዩ አገራት የተለያዩ ታዋቂ ግለሰቦች ኢፍትሀዊነትንና መድሎን በመታገል የራሳቸውን አስተዋፆ አድርገዋል::

ለምሳሌ:- ኢትዮጵያዊው ፓትሪያርክ አቡነ ጴጥሮስ የጣልያንን ወራሪ ሀይል በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረሰውን ወረራና እንግልት በመቃወም ይታወቃሉ::

በተመሳሳይ ደጃዝማች ኡመር ሰመተር ከ1928- 1932 ዓ.ም በነበረው ሁለተኛው የጣልያን ወረራ ወቅት ወራሪውን መቃወም ብቻ ሳይሆን ሌሎች የምዕራብ አውሮፓ ወራሪ ሀይላትን ለፍትህ ሲሉ ታግለው ነበር፡ ፡ እንዲሁም ታዋቂው የደቡብ አፍሪካ የነጻነትና ሰብአዊ መብት ተሟጋች ኔልሰን ማንዴላ በሀገራቸው ደቡብ አፍሪካ ዜጎች የቀለም ልዩነት ሲደረግ የነበረውን አድሎና መገለል በመቃወም ሲታገሉ ነበር፡፡ በአሜሪካም በጥቁር አሜሪካዊ ዜጎች ላይ ይደረግ የነበረውን አድሎና ማግለል በመቃወምና በመታገል የሚታወቀው ማርቲን ሉተር ኪንግ ለፍትህዊነት የራሱን አስተዋጾ በማድረግ ይታወቃል፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የፍትህ ታጋዮች ኢትዮጵያዊው ፓትሪያርክ አቡነ ጴጥሮስ፣ ደጃዝማች ኡመር ሰመተር፣ ኔልሰን ማንዴላ እና ማርቲን ሉተር ኪንግ ከዚህ በታች ምስላቸው በተከታታይ ተገልጿል፡፡



ምስል 3.1 አቡነ ጴጥሮስ



ምስል 3.2 ደጃዝማች ኡመር ሰመተር



ምስል 3.3 ኔልሰን ማንዴላ



ምስል 3.4 ማርቲን ሉተር ኪንግ

ተግባር 1፡- የሚከተለውን ጥያቄ በቡድን በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን መልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

1. በማህበረሰባችሁ ውስጥ እንደ ኢትዮጵያዊው ፓትሪያርክ አቡነ ጴጥሮስ፣ ደጃዝማች ኡመር ሰመተር፣ ኔልሰን ማንዴላ እና ማርቲን ሉተር ኪንግ የመሳሰሉ ለነጻነት ታግለው ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን ታውቃላችሁ?

### 3.1.1. የፍትሃዊነት ጽንሰ ሀሳብ

ፍትሃዊነት ማለት ሁሉንም ሰው በእኩልነት፣ በእውነተኝነት እና በማክበር እኩል እድል በመስጠት ወይም በማመቻቸት ውጤታማ እንዲሆኑ ወይም እርስበርስ በመተባበር ልዩነትን በጸጋ በመቀበልና ለዚህም ዋጋ መስጠትና ሌሎች ያለአግባብ ተጽእኖ እንደማይደረግባቸው ማረጋገጥ ነው፡፡

ታዋቂዋ እናት ማዘር ትሬዛ ሰዎችን በእኩልነትና ያለአድሎ በማየት በተምሳሌትነት ይታወቃሉ፡፡ አለምም ለሰው ልጅ ያላቸውን ገደብ የለሽ ፍቅርና ትህትና ወይም በጎነት በመገንዘብ እውቅና ሰጥቷቸዋል፡፡ በዚሁ መሰረት እኛም እንዴት አድርገን ከኛ ፍቅርና እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎችን ያለምንም የዘር፣ የእምነት፣ የቋንቋና ሌሎችንም ልዩነቶችን ሳናደርግ ሁሉንም በእኩልነት ማገልገል እንዳለብን አስተምረውናል፡፡



ምስል 3.5 ማዘር ትሬዛ

ተግባር 2፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን መልስ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

1. በማህበረሰባችሁ ውስጥ እንደ ማዘር ቴሬዛ ታዋቂና ለሁሉም ሰው እኩል እድል በመስጠት ስኬታማ እንዲሆኑ ያስቻሉ ወይም ያበቁ አሉ? ካሉ ማን ይባላሉ?

2. ከማዘር ቴሬዛ ምን ተማራችሁ?

### 3.1.2. የፍትሀዊ ሰው መገለጫዎች

ፍትሀዊ ሰው የሚከተሉት ባህሪያት አሉት

- ✓ ፍትሀዊ ሰው ምክንያታዊ ነው፡፡ ይህ ማለት ስነ-አመክንዮዊ ግልፅና በጎ እሳቦት አለው፡፡ በአንድ ነገር ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት የነገሮችን አሉታዊና አወንታዊ ጎኖችን ይፈትሻል፡፡
- ✓ ፍትሀዊ ሰው ሀሳብን ለመቀበል ዝግጁ አእምሮ አለው፡፡ ይህ ማለት ታጋሽ ነው፤ አግላይ አይደለም፣ የሌሎችን ሀሳብ ይቀበላል፡፡ በተጨማሪም የራሱን ሀሳብ ሌሎች እንዲቀበሉት አያስገድድም፡፡
- ✓ ፍትሀዊ ሰው ገለልተኛ ነው/ አይወግንም፡፡ ይህ ማለት ሁሉንም ሰው እውቀታቸውን፣ የሀብት ደረጃቸውን ወይም ማህበራዊ ማዕረጋቸውን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ሁሉንም እኩል ይቀርባል፡፡

**ወይዘሮ መአዛ**

ወይዘሮ መአዛ የሁለተኛ ክፍል ሂሳብ መምህርት ናቸው፡፡ ተማሪዎቻቸው በወላጆቻቸው የሀብት መጠን፣ አስተሳሰብ፣ እድሜ፣ ፆታ፣ ፍላጎት እንዲሁም በችሎታቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ ይሁንና ወይዘሮ መአዛ ሁሌም ተማሪዎቻቸውን በክፍል ውስጥ ያለአድሎ እኩል ይቀርቧቸዋል፡፡ እንዲሁም ለተማሪዎች ጥያቄ ሲጠይቁ ለሁሉም እኩል እድል ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቻቸው መልስ ሲመልሱ ያበረታቷቸዋል፤ ያደንቋቸዋል፡፡

ተግባር 3፡- ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች ከላይ በተሰጠው ምንባብ መሰረት በቡድን በመሆን ተወያዩ፡፡

1. ወይዘሮ መአዛ ፍትሀዊ መምህርት ናቸውን? ለምን?
2. ወይዘሮ መአዛን ፍትሀዊ መምህርት ያደረጋቸው ምንድንነው?
3. ወይዘሮ መአዛ ሁሉንም ሀሳብ ለመቀበል የተዘጋጁ መምህርት ናቸው?

## 3.2.የፍትሀዊነት አስፈላጊነት

ፍትሀዊነት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም ሰው፣ ጠንካራ፣ ውብና አንድ የሆነ ማህበረሰብ ለመገንባት "እያንዳንዱ ሰው በመከባበርና በአንድነት መስራት አለበት" የሚለውን መመሪያ ወይም ህግ መከተል ወይም ማክበር አለበት፡፡ ሰዎች እርስበርሳቸው በፍትሀዊነት የሚቀራረቡ ከሆነ እምነት ወይም መተማመንን ያጎለብታሉ፡፡

ተግባር 4፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድጥንድ ሆናችሁ ተወያዩና መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ

1. ይህ ነገር ፍትሀዊ አይደለም ብላችሁ ታውቃላችሁ? ኢፍትሀዊ መሆኑን እንዴት አወቃችሁ?
2. በሰው ተጭበርብራችሁ ወይም ተታላችሁ ታውቃላችሁ? ሲያታልሏችሁ ወይም ሲያጭበረብሯችሁ ምን ተሰማችሁ?

### ትምህርት ቤት ጓደኞች

ሮዛ፣ ፋጡማና ራሄል የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው:: በአብዛኛው በምሳ ሰዓት አብረው ይጫወታሉ:: ሁሌም ሲጫወቱ የጨዋታውን ህግ አክብረው ነው:: ነገርግን ሮዛ በዘልማድ ተራዋን ሳትጠብቅ ፋጡማና ራሄልን በማጭበርበር ሁለቴ ትጫወታለች:: በመጨረሻም ራሄል ከሮዛ ጋር መጫወቱን አቆመች:: ራሄል ለፋጡማ ሮዛ እንዴት እንዳጭበረበረቻቸው ስትነግራት ፋጡማም ተናደደች:: በመጨረሻም ስላላመኗት ሁለቱም ከሮዛ ጋር የተሰጣቸውን ተጨማሪ ስራና መጽሐፍ ማንበብ አቆሙ::

ተግባር 5፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በተሰጠው ጽሁፍ መሰረት በመወያየት መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ::

1. ፋጡማና ራሄል በሮዛ ላይ ለምን ተበሳጩ?
2. ፋጡማና ራሄል የተሰጣቸውን ተጨማሪ ስራ ከሮዛ ጋር መስራትና መጽሀፍ ማንበብ ለምን አቆሙ?
3. ሮዛን ብትሆን/ኝ ምንታድርግ/ጊ ነበር?
4. ሮዛ የጨዋታውን ህግ ያልተከተለችው ለምንድን ነው?
5. ፋጡማና ራሄል ለሮዛ ፍትሀዊ ናቸው? ለምን?

## 3.3.የፍትሀዊ ሰው ባህሪያት

ማነቃቂያ ጥያቄ፡- የሚከተለውን ጥያቄ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበት

1. ፍትሀዊነትንና የሌላውን ሀሳብ ለመቀበል ዝግጁ መሆን ጠቃሚ ነው? ለምን?

የሰዎችን ሀሳብ ለመቀበል ዝግጁ መሆን ጥቅም አለው፡፡ ምክንያቱም አብዛኛዎቹ አመለካከቶቻችንና እምነቶቻችን ምክንያታዊ ያልሆኑ እና በሌሎች ሰዎች ሀሳቦች ተፅእኖ ስር የወደቁ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው፡፡

**ፍትሓዊ አመለካከት ያላት ፌቨን**

ሃዋ፣ናቲና ፌቨን የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ሃዋ ስለምትናገረው ነገር ግድ የላትም፡፡ የምትፈልገውን ነገር ደስ እንዳላት ታደርጋለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ናቲ በአስተሳሰቡ በጎ ነው፡፡ ነገር ግን ስለሌሎች ፍትሀዊ አይደለም፡፡ ብቻውን መስራት ይወዳል፡፡ የሌሎችን ሀሳብ አያዳምጥም፣ ያለውን ንብረት ለሌሎች አያካፍልም፡፡ ነገር ግን ፌቨን በአስተሳሰቧ ጥሩና የማታዳላ ሀቀኛና የተሟላ ስብዕናና ችሎታ አላት፡፡ በዚህም ታማኝነትን ከማጥፋት ይልቅ ለማጎልበት የምትጥር ስትሆን ታጋሽና ሰዎችን የማታበላልጥ ናት፡፡

ተግባር 6፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በተሰጠው ምንባብ መሰረት መልሱ፡፡ መልሳችሁንም በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

1. የማያዳላ ባህሪ ያለው ማነው?
2. ፌቨን ለጓደኞቿ ፍትሀዊ ናት? ለምን?
3. ናቲ ለጓደኞቹ ፍትሀዊ ነው? ለምን?
4. ከሶስቱ ተማሪዎች መካከል የየትኛውን ስብዕና ወደዳችሁት? ለምን?

## 3.4.የፍትሀዊነት አለመኖር ውጤቶች

በማህበረሰባችሁ ውስጥ ፍትሀዊነት ባይኖር ምን ሊከሰት እንደሚችል አስቡ፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች አይግባቡም፣ እርስበርሳቸው ይጋጫሉ፣ በጋራ አይሰሩም ስለዚህ ለመኖር ይቸገራሉ፡፡

ነገር ግን ሰዎች እኩል ወይንም በፍትሀዊነት በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ሁሉም በጋራ ይሰራሉ፣ ችግሮቻቸውን በቀላሉ ይፈታሉ፣ይጫወታሉ፣ ይረዳዳሉ፣ ደህንነትም ይሰማቸዋል፤ ረጅም ጊዜም ይኖራሉ። ይህ ነው ብዙ ሰው እንዲኖረው የሚፈለገው

### ርዕሰ መምህር ሀይሉ

አቶ ሀይሉ የመንግስት ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ናቸው። ተማሪዎችና መምህራን ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የትምህርት ቤቱን ደንብና መመሪያ አይከተሉም። ለምሳሌ ተማሪዎች የደንብ ልብሳቸውን ሳይለብሱ ወደ ትምህርት ቤት ይመጣሉ። የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ አርፍደው ይመጣሉ። መምህራንም የደንብ ልብስ የሚለብሱት ወደ መማሪያ ክፍል ሲገቡ ብቻ ነው። አንዳንዶቹ ደግሞ ይህንንም አይተገብሩም።

የተወሰኑ ተማሪዎችና መምህራንም የደንብ ልብስ የማይለብሱ መምህራንና ተማሪዎችን እንደ አርአያ እየቆጠሩ ነው። በተጨማሪም መምህራን እርስበርሳቸው አይተባበሩም። እንዲሁም ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህርና በአንዳንድ መምህራን በፍትሀዊነት እንደማይስተናገዱ ያስባሉ። በመጨረሻም ይህ ሁኔታ ተማሪዎች እርስበርሳቸው እንዳይተባበሩ ፣ ችግርን የመፍታት ክህሎት እንዳይኖራቸው፣ ለሌሎች ደህንነትና ስሜት ግድየለሽ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

ተግባር 7:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በተሰጠው ፅሁፍ መሰረት ተወያዩባቸው።

1. አንዳንድ ተማሪዎች ለምን የደንብ ልብስ ከማይለብሱ ተማሪዎች ጋር መቀላቀል ፈለጉ?
2. ተማሪዎች ለምን የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህርና አንዳንድ መምህራን በፍትሀዊነት እንደማያይዋቸው ተሰማቸው?
3. መምህራን በትምህርት ቤት ለምን እርስበርሳቸው አይተባበሩም?
4. በትምህርት ቤቱ ውስጥ ተመሳሳይ ደንብ አለመኖሩ በስተመጨረሻ ተማሪዎችን ምን አደረጋቸው?

## 3.5.ኢፍታዊነትን መታገል

**ለፍትህ የቆመ ተምሳሌታዊ ግለሰብ**

ለራስ ህግን ማክበርና መተግበር ኢፍትህዊነትን ለመታገል የመጀመሪያው መንደርደሪያ ነው፡፡ ይህ ሊከብድ ይችላል ነገር ግን በተቻለ መጠን ኢፍትሀዊ ለሆነ ነገር ምንም አስተዋፅዖ አለማድረግና ከዛ ይልቅ ፍትሀዊ ባህሪን ለመላበስ መሞከር ነው፡፡

**ተግባር 8፡- የሚከተለውን አጭር ትረካ ካነበባችሁ በኋላ በተሰጡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ፡፡**

**የክፍል ጓደኛሞች**

ጉቱና ሀናን የሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ቀን ጉቱ እርሳሱን ረስቶ ወደ ትምህርት ቤት መጣ፡፡ በመቀጠልም የሂሳብ መምህራቸው ወደ ክፍል ሲገቡ ጉቱ በፍጥነት የሃናን እርሳስ እንደራሱ ከቦርሳዋ ውስጥ ወሰደ፡፡ ነገር ግን አለሙ ጉቱ ከሀናን ቦርሳ እርሳስ ሲወስድ ይመለከተው ነበር፡፡ ምንም እንኳን አለሙ የጉቱ ጓደኛውና ጎረቤቱ ቢሆንም ሀናን ጉቱ እርሳሷን እንደወሰደባት ለመምህሩ ነገራቸው፡፡ ይሁን እንጂ ጉቱ አለመውሰዱን ለመምህሩ ክዶ ተናገረ፡፡ ይህ የኔ እርሳስ ነው ብሎ አስረዳ፡፡ ቢሆንም አለሙ የጓደኛውን የጉቱን ውሸታምነት ሊታገስ አልቻለም፡፡ እናም እርሳሱ የሀናን መሆኑን ለመምህሩ አስረዳቸው፡፡ በመጨረሻም መምህሩ ጉቱ የሀናንን እርሳስ በፍጥነት እንዲመልስ አደረጉት፡፡

1. ከጉቱ ድርጊት ምን ተማራችሁ?
2. ከመምህሩ ድርጊት ምን ተማራችሁ?
3. ከአለሙስ ድርጊት ምን ተማራችሁ?
4. አለሙን ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?
5. ጉቱ ጓደኛችሁ ቢሆን ትተባበሩት ነበር? ለምን?

ተግበር 9፡- ከዚህ በታች ያለውን ትረካ አንብቡና በምንባቡ መሰረት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

አንድ ቀን አቶ ሮባ ከክፍሉ ተማሪዎች በቁጥር 5 የሚያንስ ከረሜላ የያዘ እሽግ ይዞ መጣ፡፡ ከዛም ለክፍሉ ተማሪዎች የከረሜላ እሽጉን ሰጥቶ እያንዳንዱ ተማሪ አንድ አንድ ከረሜላ እንዲወስዱ ነገራቸው፡፡ በመጨረሻም ከረሜላ ያልደረሳቸው ተማሪዎች ከረሜላው ከተማሪው ቁጥር እንደሚያንስ በተረዱ ጊዜ እንዳልተፈለጉና እንደተገለሉ ተሰማቸው፡፡

1. ከረሜላ ያልደረሳቸው ተማሪዎች ምን ሊሰማቸው ይችላል?
2. ለችግሩ ፍትሀዊ መፍትሄ ምን ሊሆን ይችላል?
3. ሰዎች አለአግባብ ሲስተናገዱ የሚሰማቸው ሌላ ተመሳሳይ የመገለልን ስሜት ልታስቡ ትችላላችሁ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር ስለ የፍትህ ምንነት፣ አይነቶች፣ የፍትሀዊነት አስፈላጊነት፣ ሚዛናዊ ወይም የማያዳላ ሰው ባህሪያት፣ የፍትህ እጦት ውጤትንና ኢፍትሀዊነትን ለመታገል መቆምን አይተናል። ይህንን በማድረግ ፍትህ ለሰው ልጆች አብሮ መኖር አስፈላጊ መሆኑን፤ በተጨማሪም ሚዛናዊነት ወይም አለማዳላትና ሚዛናዊ የሆነ ሰው ለማህበረሰቡ አስፈላጊ መሆኑን ተምራችኋል። ምክንያቱም ሚዛናዊነት ከሌለ ግጭት በሰዎች መካከል ሊከሰት ይችላል። ስለዚህ ብቻችሁን እንኳን ብትሆኑ በፍትህዊነት መቆም ይገባችኋል።

## የምዕራፍ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ አረፍተ ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ::

1. ለፍትህ የሚቆም ሰው መደነቅ አለበት::
2. ፍትህዊነትወይም አለማዳላት ማለት ሁሉንም ሰው በእውነተኛነትና በክብር መመልከት ነው::
3. ፍትህዊነት ለማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ለራስም አስፈላጊ ነገር ነው::
4. ህግን ለራስህ ብለህ ስታከብር እንደ ኢፍታህዊነት ይቆጠራል::
5. ሚዛናዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ሩህሩህ ናቸው::

II. ከዚህ በታች ለተቀመጡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ከሚከተሉት ውስጥ የፍትሀዊ ሰው ባህሪ የቱ ነው?
   ሀ. ፍትሀዊ ሰው ምክንያታዊ ነው
   ለ. ፍትሀዊ ሰው የሌሎችን ሰዎች ሀሳብ ይቀበላል
   ሐ. ፍትሀዊ ሰው ገለልተኛ ነው
   መ. ሁሉም
2. ፍትህ በሰፈነበት ማህበረሰብ ውስጥ ሰዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?
   ሀ. አንዱ ለሌላው ይጠነቀቃል
   ለ. ደህንነት ይሰማቸዋል
   ሐ. አብሮ መስራትን ይወዳሉ
   መ. ሁሉም

3. ከሚከተሉት ውስጥ የፍትሀዊ ሰው ባህሪ ያልሆነው

ሀ. የሌላውን ሰው ሀሳብ ለመቀበል ዝግጁ ነው

ለ. ምክንያታዊ ነው

ሐ. ምክንያታዊ አይደለም

መ. ፍትሀዊ ነው

4. ፍትህ በሌለበት ማህበረሰብ ውስጥ ምን ይከሰታል?

ሀ. ሁሉም ሰው ይተማመናል

ለ. ሰዎች በጋራ አይሰሩም

ሐ. ሰዎች ችግራቸውን በቀላሉ ይፈታሉ

መ. ሁሉም

5. ኢፍትሀዊነትን መታገል ለማህበረሰቡ ምን ይጠቅማል?

ሀ. ለመተባበር

ለ. ፍትሀዊነትን ለማበረታታት

ሐ. እርስ በርስ ለመተማመን

መ. ሁሉም

# ምዕራፍ አራት

## አወንታዊ ማኅበራዊ መስተጋብር

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች:

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- የማህበራዊ መስተጋብር ምንነትን ታስረዳላችሁ
- ማህበራዊ መስተጋብር በትምህርት ቤትና በማህበረሰቡ ውስጥ እንዴት እንደሚጎለብት እውቅና ትሰጣላችሁ
- ማህበራዊ መስተጋብር ለተማሪዎች መማር ያለውን ጠቀሜታ ዋጋ ትሰጣላችሁ
- የማህበራዊ መስተጋብር እንቅፋቶችን ትለያላችሁ
- በጎ የሆነ የአቻ ላቻ ማህበራዊ መስተጋብር ትተገብራላችሁ።

### 4.1.የአወንታዊ ማህበራዊ መስተጋብር ምንነት

የማነቃቂያ ጥያቄ:-

ውድ ተማሪዎች:-

1. በትምህርት ቤታችሁ የቅርብ ጓደኛ አላችሁ?
2. በምን ምክንያት ነው የቅርብ ጓደኛ ያደረጋችሁት?
3. ጓደኝነት ምን ጥቅም አለው?

እንደ ማንኛውም የሰው ልጅ ሁላችንም ማህበራዊ መስተጋብርን ከተለያዩ ሰዎች ለምሳሌ ከወላጆቻችን፣ ከእህቶቻችን፣ ከወንድሞቻችን፣ ከዘመዶቻችን እና ከጓደኞቻችን፣ ከጎረቤታችን እንዲሁም ከክፍል ጓደኞቻችን ጋር የመፍጠር ተፈጥሮአዊ ፍላጎት አለን። በመልካም ጓደኝነትና የእርስ በርስ ፍላጎትን ባረካ መልክ የሚመሰረት ማህበራዊ ወዳጅነት በጎ ማህበራዊ መስተጋብር ይባላል።



ምስል 4.1 የክፍል ጓደኞች በትምህርት ቤት መጫወቻ ቦታ ላይ ሲጫወቱ



ምስል 4.2 ልጆች ከወላጆቻቸው  ጋር የእንሰሳት ማቆያ ሲጎበኙ

ተግባር 1፡- ከላይ የተቀመጠውን አጭር ጹህፍ መሰረት በማድረግ መጀመሪያ የማህበራዊ ግንኙነትን ጠቀሜታን በወረቀት ላይ ጻፉ በመቀጠል ከጓደኞችሁ ጋር በመቀያየር የሰራችሁትን መልስ አነጻጽሩ፡፡

## ሳራና ሀሊማ - አዲስ ጓደኝነት እየመሰረቱ ነው።



ምስል 4.3 ሳራና ሀሊማ ሰላምታ እየተሰጣጡ

ሳራ - እንደምን አደርሽ ሃሊማ?

ሃሊማ- እንደምን አደርሽ ሳራ?

ሳራ- በክፍላችን ውስጥ የቅርብ ጓደኛ የለኝም የቅርብ ጓደኛዬ ልትሆኚኝ ፍቃደኛ ነሽ?

ሃሊማ- ሳራ እኔም የቅርብ ጓደኛ የለኝም። እናም ደስተኛ ነኝ የጓደኝነት ጥያቄሽን እቀበላለሁኝ ነገር ግን የጥሩ ጓደኝነት መግለጫዎችን ልትነግሪኝ ትችያለሽ?

ሳራ- አመሰግናለሁ ሃሊማ- ጥሩ ጓደኛ ማለት የጋራ ፍላጎት ፣ዝንባሌና ጥሩ ጊዜ ማሳለፊያ የሚያውቅ/ታውቅ፣ ንብረቱን በጋራ የሚጠቀም/የምትጠቀም፣ አብረሽ ስትጫወቺ የሚመችሽ/የምትመችሽ ነው። አንቺስ የጥሩ ጓደኛ መግለጫዎችን ልትነግረኝ ትችያለሽ?

ሃሊማ- በእርግጠኝነት ሳራ - ያንቺን ምርጫ ስለነገርሽኝ አመሰግናለሁኝ አንቺ ከዘረዘርሽልኝ በተጨማሪ ለጓደኞቹ ጥንቃቄ /ጠንቃቃ/ መሆን አለበት

ሳራ- የሚገርም ነው- ሃሊማ አንቺ ድንቅ ነሽ ለአንቺና ለሌሎችም ጥሩ ጓደኛ ለመሆን እሞክራለሁ፤

ሃሊማ- አመሰግናለሁኝ፣

ሳራ- ምንም አይደል፣ ምልልሱን እንዳነበባችሁት ሳራና ሃሊማ ማህበራዊ መስተጋብር ለማሳደግ ጥሩ ጓደኝነት ስላለው አስተዋፆ ተወያይተዋል።

ተግባር 2፡- ከላይ በተገለጸው ምልልስ መሰረት ከታች ያሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ መልሱ?

1. የጥሩ ጓደኝነት መገለጫዎች ምንድን ናቸው?

2. ጥሩ ጓደኛ የሚያደርጉህ/ሽ መልካም ባህሪ ያት የትኞቹ ናቸው?

## ማህበራዊ ክህሎት

ማህበራዊ ክህሎት ማለት ከምናገኛቸው ሰዎች ጋር ለምንፈልገው ወይም ለምንመሰርተው ጤናማ፣ ዘላቂ፣ ተገቢነት፣ጥሩ ግንኙነት ለመመስረትና በጎ ውጤት ለማምጣት የሚያስችል ባህሪና ክሕሎት ነው። እነዚህም ባህሪያት ተግባቢነት፣ ሰላምታ መስጠት፣ መተባበር፣ ሌላውን በችግር ግዜ መርዳት ናቸው።



ምስል 4.4 የክፍል ጓደኛሞች አሻንጉሊት በጋራ ሲሰሩ



ምስል 4.5 ልጅቷ የተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚ ጓደኛዋን ስትረዳው

ተግባር 3፡- ተማሪዎች ከላይ ከተሰጠው ማብራርያ ምን ተማራችሁ?

ተማሪዎች ማወቅ ያለባችሁ ነገር መተባበር ለማህበራዊ ግንኙነት በጣም ጠቃሚ መሆኑን ነው፡፡ እርግጥ ሰዎች የተለያየ ተሰጥዖና ክህሎት አላቸው፡፡ ስለዚህ በተባበሩ ቁጥር ለጋራ ግብ አስተዋፆ አላቸው፡፡ ትብብር አንዱ የማህበራዊ ግንኙነት መሠረትና አብሮነት ምንጭ ነው፡፡ አንድነት ጥንካሬን ያመጣል፡፡ ነገር ግን መከፋፈል ውድቀትን ያመጣል፡፡ ከዚህ በታች ያለው አጭር ትረካ ይህንን ያመለክታል፡፡

### ሦስት ልጆችና የታሰሩ ዱላዎች

ከእለታት አንድ ቀን አንድ አዛውንት ከሦስት ልጆቻቸው ጋር በትንሽ የገጠር መንደር ይኖሩ ነበር፡፡ ሁሉም ወንድማማቾች ጠንካራ ሠራተኞች ናቸው፡፡ ነገር ግን አብሮ መሥራትን አይወዱም ነበር፡፡ ሁሌም ይጣላሉ፡፡ ስለዚህ አባትዬው ልጆቻቸው በአንድነት እንዲቆዩ ብዙ ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም፡፡ ሽማግሌው ታመሙ፡፡ ይሁንና ወንድማማቾቹ አሁንም አባትዬውን እንደከዚህ ቀደሙ ምክራቸውን ለመቀበል አልፈለጉም፡፡ ስለዚህ አባትዬው ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸው ልዩነትን አስወግደው በአንድነት የሚኖሩበትን ትምህርት ለመስጠት አሰቡ፡፡

ስለዚህ ሦስቱን ልጆቻቸውን ጠሩና በአንድ ላይ የታሰረ የዱላ ሥር ለእያንዳንዳቸው ሰጧቸውና “ስበሩ” አሉአቸው፡፡ እና የታሰሩትን ዱላዎች ቀድሞ ሰብሮ ለጨረሰ ሽልማት እንደሚሰጡ ቃል ገቡ፡፡ ልጆቹም በታዘዙት መሠረት ዱላዎቹን በፍጥነት ለመስበር እና ማን ቅድሚያ እንደሚመጣ ባለመስማማት ተጣሉ፡፡ አባትዬውም ልጆቹ “ጨዋታው አላለቀም አትጣሉ” አሏቸው፡፡ ለሁላችሁም እስር ዱላዎችን እሰጣችሁና እናንተም እንደታሰረ ትሰብራላችሁ” አሏቸው፡፡

ነገር ግን ልጆቹ የታሰሩ የዱላዎቹን በተናጥል ለመስበር ሞክረው አልቻሉም። በመጨረሻም አባትዬውም - “ልጆቼ ልብ በሉ ነጠላ ዱላውን በቀላሉ ለመስበር ቻላችሁ። ነገር ግን የታሰሩ ዱላዎችን ለመስበር ሞክራችሁ አልቻላችሁም። ይህ የሚያሳየው አንድ ስትሆኑ ማንም እናንተ ላይ ጉዳት አያደርስም። ነገር ግን ሁሌም የምትጣሉ ከሆነ ማንም ይተናኮሏችሁና ያሸንፋችኋል። ስለዚህ ምክር ልለግሳችሁ፡- በአንድነት ኑሩ”። በመጨረሻም ሦስቱ ወንድማማቾች መተባበር ጉልበት መሆኑንና ለአባትዬውም በትብብር እንደሚዘልቁ ቃል ገቡላቸው።

ተግባር 4፡- ከላይ ከተቀመጠው አጭር ትረካ ምን ትምህርት ወሰዳችሁ?

ከዚህ በታች የተሰጠው የማህበራዊ ክህሎት ለበጎ ማህበራዊ መስተጋብር ምሳሌ ነው።

| ትንሽ ምክር ስለ ማኅበራዊ ክህሎት | እንዴት እንደሚገለጹ |
|---|---|
| ቀስቃሽ ሀሳቦችን ማፍለቅ | ምስራቅ ወደ ዱር እንስሳት መጠበቂያ እንሂድ |
| የአቻ ጓደኛን ግብዣ ተቀብሎ መቀላቀል | እሺ ከማል እቀላቀላችኋለሁ |
| የጓደኛን ትኩረት ማግኘት | አዜብ እንቆቅለሽ እንጫወት |
| ዕቃን መጋራት | አለሚቱ እነዚህ የእኔ ትርፍ ቀለማት ስለሆኑ መጠቀም ትችያለሽ |
| ጓደኛን ዕቃ እንዲያጋራ መጠየቅ | ሙሴ እርሳስህን መዋስ እችላለሁ? |
| በጎ ነገር ለጓደኛ መንገር | መልካም ቀን ፎዚያ |
| ምስጋና | አመሰግናለሁ አድናቂህ ነኝ |
| ትሕትና | ወደ መጸዳጃ ቤት ልሂድ |

በተቃራኒው ከላይ የተገለጹትን ማኅበራዊ ክህሎቶች የሌላቸው ተማሪዎች እነዚህን የሚጎዱ ባህሪያት ያሳያሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ድርጊቶች አለመተግበርና ጥሩ ልምድና ማኅበራዊ መስተጋብሮችን የሚያሳድጉ ባህሪያትን እንደ ትብብር፣ ይቅር ባይነት፣ ቸርነት እና ሌላውን መርዳት፣ ለሌላው ጥሩ ማድረግ ሁሌም ይክሳል፡፡ በጎ ጎኖችንና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ላይ መመርኮዝ ይገባል፡፡

ተግባር 5፡- ስለማኅበራዊ ክህሎቶች የሰጡትን ምሳሌ መሰረት በማድረግ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተቀባይነትና ተቀባይነት የሌላቸውን ማኅበራዊ ግኑኝነቶች ዘርዝሩ፡፡

## 4.2. አወንታዊ ማኅበራዊ መስተጋብሮችን ማሳደጊያ መንገዶች

መልካም ግንኙነትን ከአቻና ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመጀመርና ለማጽናት የሚረዱ የተለያዩ ዕቅዶች ወይም ዘዴዎች አሉ፡፡

የመጀመሪያ ዘዴ ግንኙነትን ከቃላት ውጪ መጀመር ነው፡፡ ለምሳሌ የዓይን ጥቅሻ፣ እርጋታን ማሳየት፣ሳቢ ጓደኛዊ የአካል እንቅስቃሴ ማሳየት፣ ይህ ንግግር አልባ መግባባት ለጓደኞችን ያለንን ፍላጎት ያሳያል፡፡

ሁለተኛው ዘዴ መደበኛ የመረጃ መለዋወጥ ይህም በሁለት አቅጣጫ መግባባት ነው፡፡ ይህም አሁን ከምንመሠርተው ጓደኛ ጋር ጠለቅ ያለ መረጃ እንለዋወጥበታለን፡፡ ለምሳሌ ስለ ዕድሜ፣ ሥም፣ መኖሪያ አድራሻ፣ የምንጠላውንና የምንወደውን ፍላጎት ማወቅ፡፡

- ✓ ለምሳሌ “እንዴት ነህ፣ ስሜ ረጋቱ ነው፡፡ ያንተስ ስም ማነው?

ተግባር 6፡- ሁለት ፍቃደኛ ተማሪዎች ስለ መልካም ጓደኛ የሚወዱትና የሚጠሉትን ባህርያት በሚና ጨዋታ ክፍል ውስጥ ይተግብሩ፡፡

ስለእያንዳንዳችን ጠለቅ ያለ እውቀት በግልጽነት ካወቅን ዘላቂነት ያለው ጓደኝነትን ለመመሥረት ይጠቅመናል፡፡

ሦስተኛው ዘዴ በግልጽነት የሚያመሳስሉትንና ልዩነቶችን በጓደኞሞች መካከል ለማወቅ ይረዳናል፡

አራተኛው ዘዴ በቡድን በመሥራት ማኅበራዊ ክህሎቶችን ማዳበር ፡፡

## 4.3.የአወንታዊ ማህበራዊ መስተጋብሮች አስፈላጊነት

ከዚህ በላይ ባለው የትምህርት ይዘት መልካም ጓደኝነትን እና ተገቢ የሆኑ ማህበራዊ ትስስሮችን በማጎልበት የማህበራዊ ክህሎትን ማዳበር የሚቻልባቸውን መንገዶች እና ዘዴዎችን ተምራቹኋል፡፡ በዚህ የትምህርት ይዘት የአወንታዊ ማህበራዊ መስተጋብሮች ጥቅምን ትማራላችሁ፡፡ በጎ ማኅበራዊ መስተጋብር ከሌሎች ሰዎች ጋር መመሥረት በርካታ ጠቄሜታዎች አሉት፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጥብቅ ጓደኝነትን በመፍጠር የሃሳብ መጋራት እንዲሰፍንና የብቸኝኘነት ስሜት እንዳይሰማን ይረዳል፡፡ መልካም ጓደኝነትን ለመመስረት ታማኝነትን፣ ቸርነትን፣ እውነተኛነትን፣ ይቅር ባይነትን ፣መሥዋዕትነት መክፈልን ይፈልጋል፡፡ እነዚህ የመልካም ጓደኝነት መለያ ባህርያት ችግሮችን ለመቅረፍ ይረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ማኅበራዊ ክህሎቶችን፣ እውቀትንና ግብረ-ገባዊ ዕሴቶችን ለመማር ይጠቅማሉ፡፡

ተግባር 7፡- ከላይ በተገለፀው ፅሁፍ መሰረት የበጎ ማህበራዊ መስተጋብር ጠቀሜታን ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ፃፉ፡፡ እንዲሁም በግላችሁ ሁለት ተጨማሪ የበጎ ማህበራዊ መስተጋብር ጠቀሜታን ደብተራችሁ ላይ በመፃፍ መልሱን ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## 4.4.የአወንታዊ ማኅበራዊ መስተጋብር እንቅፋቶች

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. ውድ ተማሪዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር ስትጫወቱ ችግር አጋጥሟችሁ ያውቃል?
2. ለችግሩ ተጠያቂ ማነው?
3. ችግሩን እንዴት ለመፍታት ሞከራችሁ?

ከዚህ ቀደም በነበረው የትምህርት ክፍል ስለ በጎ ማኅበራዊ መስተጋብር ጥቅም ተምራችኋል። ይሁን እንጂ  መልካም ማኅበራዊ መስተጋብርን ለመመስረት የሚያግዱ እንቅፋቶች መኖራቸውን መረዳት አስፈላጊ ነው። ከነዚህ ባህርያትና ድርጊቶች የሚከተሉት ዝርዝር ምክንያቶች እንደ ምሳሌ ሊታዩ ይችላሉ።

- ሰውን አለማክበር
- አለመታመን
- ሰውን ማዋረድ
- የሰውን ቁስ መፈለግ
- በሰልፍስነ-ስርአት መገፋፋት
- አለመተባበር
- ብቸኝነት
- አይናፋርነት
- ደንቦችን መጣስ
- ቁጡነትና ሌሎችን መበጥበጥ
- ስግብግብነትና ራስ ወዳድነት

ከላይ የተገለጹት ሁሉም ባህሪያት በጎ ማኅበራዊ መስተጋብሮችን ያውካሉ። ለምሳሌ ቸርነት ይክስሀል። ስግብግብነት ሌሎችን ከማስቆጣት በተጨማሪ



ምስል 4.6 ውሻው የራሱ ምስል ወንዝ ውስጥ ሲያይ

## ስግብግቡ ውሻ

ከእለታት አንድ ቀን በአንድ አነስተኛ የገጠር መንደር ውስጥ የሚኖር ውሻ ነበር፡፡ ይህ ውሻ ተርቦ ስለ ነበር ለአደን ወጥቶ አነስተኛ ጥንቸል አድኖ በመያዝ የሚችለውን ያህል ከበላ በኃላ የተረፈውን አጥንት በአፉ ይዞ ወደ መኖርያ ቤቱ ሲመለስ በአነስተኛ ወንዝ ላይ የተሰራ ድልድይ አጋጠመው፡፡ በሚሻገርበት ወቅት ሌላ አጥንት የያዘ ውሻን ወንዝ ውስጥ ይመለከታል፡፡ ነገር ግን በወንዝ ውስጥ የተመለከተው የራሱን ምስል መሆኑን አልተገነዘበም፡፡ በመሆኑም ይህ ስግብግብ ውሻ ከራሱ ምስል ላይ አጥንቱን ለመንጠቅ ሲጮህ በአፉ ይዞት የነበረው አጥንት ወራጅ ወንዝ ውስጥ ወደቀበት፡፡ አጥንቱም በወንዙ ተወሰደ፡፡

ተግባር 8፡- ከላይ ከተሰጠው ትረካ ምን እንደ ተማራችሁ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በጎ ማኅበራዊ መስተጋብር ሰላማዊና ወዳጃዊ ማኅበራዊ ግንኙነትን ለመመሥረት ቀና መንገድ ስለመሆኑ ተምራችኋል፡፡ እንዲሁም ዘላቂና የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ መስተጋብር ለመመስረት ጠቃሚ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አስፈላጊ የሆኑት ማህበራዊ ክህሎቶችን ለማጎልበት እና መልካም የሆነ መስተጋብርን ለመፍጠር ይረዳል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሁሉንም መለሶች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ጻፉ

ክፍል አንድ፡ አረፍተ-ነገሩ ትክክል ከሆነ እውነት ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሳችሁን ጻፉ፡፡

1. የቅርብ ጓደኝነትን ከሁሉም ጋር በቀላሉ መመሥረት ይቻላል፡፡

2. ሀሊማና ሣራ ስለ ጥሩ ጓደኝነት ባህርያት ላይ አይስማሙም፡፡

3. ስግብግብነት በጎ ማኅበራዊ ግኑኝነትን ይጎዳል፡፡

ክፍል ሁለት፡ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ ለበጎ ማኅበራዊ መስተጋብር መመስረት አስፈላጊ ያልሆንው የቱ ነው?

ሀ. ቸርነት

ለ. ታማኝ አለመሆን

ሐ. የጋራ መንፈስ

መ. ትብብር

2. ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ግጭት ውስጥ ስትገቡ ማድረግ ያለባችሁ ጥሩ ነገር ፡-

ሀ. ችላ ማለት

ለ. ተጣልቶ ማሸነፍ

ሐ. በሰላማዊ መንገድ ግጭቱን መፍታት

መ. ትምህርት ቤቱን መቀየር

4. ከሚከተሉት ውስጥ ዘላቂነትንና የጋራ ተጠቃሚነትን የማይጎዳው የትኛው ነው?

ሀ. ማክበር

ለ. ማመን

ሐ. ሰጥቶ መቀበል

መ. ሁሉም

ክፍል ሦስት፡- በዚህ ምዕራፍ የተማራችኋቸውን ትረካዎች መሰረት በማድረግ በ “ሀ” ረድፍ ለተዘረዘሩት ትረካዎች ከ “ለ” ዘርፍ ከተዘረዘሩት ተግባራት ጋር አዛምዱ፡፡

| <u>ረድፍ “ሀ”</u> | <u>ረድፍ “ለ”</u> |
|---|---|
| 1. ወንዝ ተሻጋሪ ውሻ | ሀ. ጓደኝነት ሰጥቶ መቀበልን ይፈልጋል |
| 2. ሦሥቱ ወንድማማቾች | ለ. ባለህ ነገር ተደሰት |
| | ሐ. አንድነት ጉልበት ነው |

# ምዕራፍ አምስት

## ለጋራ ጥቅም መቆም

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-
- የጋራ ጥቅም ምንነትን ትገልጻላችሁ
- ለጋራ ጥቅም መቆምን አስፈላጊነት ትወያያላችሁ
- የበጎነትን ልማድ በትምህርት ቤትና በማኅበረሰብ ውስጥ ታሳያላችሁ
- በግለኝነትና በጋራ ጥቅም መካከል ያለውን ልዩነት ታብራራላችሁ
- የጋራ ጥቅም አካላትን ትለያላችሁ
- የጋራ ጥቅም የሚጎዱ ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡

## 5.1.የጋራ ጥቅም ምንነት

የማነቃቂያ ጥያቄ

በመኖርያ አከባቢያችሁ የሚኖሩ የማህበረሰብ አካላት በጋራ የሚጠቀሟቸውን ነገሮች ግለፁ፡፡

የጋራ ጥቅም የሚለው ሀረግ ለሰው ልጆች፣ ለግለሰቦች፣ ለቡድኖች፣ ለማኅበረሰብ፣ እንዲሁም ለሀገር ሕዝብ በተጨማሪ ለዓለም ሕዝብ መገልገያነት የሚረዱ ቁሳዊ፣ ባህላዊና ተቋማዊ አካላትን የሚያሳይ እሳቤ ነው፡፡ የጋራ መጠቀሚያ ሀብት ማለት ሁሉን አቀፍ ነው፡፡ በመሆኑም ፆታን፣ ዕድሜን፣ ኃይማኖትን፣ ባህልንና የዘር ልዩነትን ሳይፈጥር ለሁሉም የሰው ልጆች ተጠቃሚነት ይውላል፡፡

የጋራ ጥቅም ማህበራዊ ደህንነትን፤ ማህበራዊ አገልግሎትን፤ሃብትን እና ማህበራዊ እሴቶችን በጋራ ለመጠቀም የሚረዱ ተቋማትን ያካተተ ነው፡፡



ምስል 5.1 ሴቶች በጋራ ከጉድጓድ ውኃ ሲቀዱ



ምስል 5.2 ትምህርት ቤት



ምስል 5.3 የሳር መሬትና ትልቅ ወንዝ

ተግባር 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩ።

ሀ. ከላይ ከተገለጹት ስእላዊ መግለጫዎች መሰረት በአከባቢው የሚኖሩ ሰዎች ምን ይጠቀማሉ?

ለ. እነዚህን በስእላዊ መግለጫዎች የተመለከቱትን ሦስት ነገሮችን ባያገኙ ምን ይሆኑ ነበር?

ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማት፣ የፖሊስ ጣቢያዎች እና መሰል ተቋማት የጋራ ጥቅም ምሳሌዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ማህበራዊ አገልግሎቶችን እንደ መብራት ሃይል፣ ንፁህ ውሃ፣ ምቹ አከባቢ፣ የመገናኛና የመጓጓዣ አገልግሎትን ለጋራ ጥቅም የሚሰጡ ሌሎች ተቋማትንም ያካትታል። እንዲሁም ማህበራዊ እሴቶቻችንን አንዱ የሌላውን ስሜት መጋራት፤ መከባበር፤ መተባበር፤ ሌላውን መርዳት፤ ልዩነትን ማክበርና መቻቻል ወዘተ ይጨምራል።

ተግባር 2. ከላይ በተሰጠው ፅሑፍ መሰረት የራሳችሁን ተጨማሪ የጋራ ሀብቶችና ጠቀሜታቸውን ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩ።

## 5.2. ለጋራ ጥቅም ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነት

የማነቃቂያ ጥያቄዎች

1. ውድ ተማሪዎች ህመም ተሰምቷችሁ ያውቃል?
2. ለህክምና የት ሄዳችሁ?

የጋራ ሀብቶች ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ሰፊው ማህበረሰብ ለሁሉም የሰው ልጅ የተለያዩ ጠቀሜታዎችን ይሰጣሉ። ከማህበረሰብ ተነጥሎ የተሻለ ህይወት መምራት አዳጋች ነው። ስለዚህ የጋራ ሀብቶች ከጋራ ስሜት፣ ፍላጎትና ደስታ በመመንጨት ህብረትና አንድነትን ይፈጥራሉ።



ምስል 5.4 ሰዎች በትልቅ ወንዝ ድልድይ ላይ ሲሻገሩ

በሁለተኛነት የጋራ ሀብቶች የሰዎች ደህንነትን ለመጠበቅ ይረዳሉ፡፡ ለምሳሌ የጋራ ሀብት ተቋማት (የፖሊስ ጣቢያ እና ፍርድ ቤት) በሌሉበት ሰላምና ደህንነት፣ ለህይወታችንና ለንብረታችን ዋስትና አይኖረንም፡፡ በሶስተኛነት የጋራ ሀብት መጠበቅና ማሳደግ ለሰው ልጆች እድገት አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ እድገት በሌላ በኩል ህይወታችንን ምቹ ያደርጉልናል፡፡



ምስል 5.5 ሌባው የልጃገረዷን ቦርሳ ሰርቆ ሲሮጥና በፖሊስ ሲያዝ

## 5.3.ለሌላ ሰው በጎ ስራ መስራት

በጎነት የሚያመለክተው ከራስ ደህንነት ይልቅ የሌላ ሰው ደህንነትን አስፈላጊ መሆኑን ማመን ነው። በጎ ሰዎች ለሌላ ሰዎች ጥሩ ነገር ያደርጋሉ። ምክንያቱም ይህን ማድረግ ግዴታ ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው። ከራሳቸው እርካታ ይልቅ ለሌሎች ጥቅም ቅድሚያ ይሰጣሉ። የበጎነት ምሳሌ የሆኑትና ትልቅ የእንክብካቤ ማእከል በአዲስ አበባ ከተማ ለወላጅ አልባ ህፃናትና ቤት አልባ የሆኑ አረጋውያንን ያቋቋሙት የቀድሞዋ የክብር ዶክተር አበበች ጎበና እና የክብር ዶክተር ቢንያም በቀለ በቅደም ተከተል ተቀምጠዋል።



ምስል 5.6 ክብርት ዶክተር አበበች ጎበና



ምስል 5.7 ክቡር ዶክተር ቢንየም በቀለ

ተግባር 3፡- ከዚህ በላይ ከተገለፁት በጎ አድራጊ ሰዎች በተጨማሪ ሌሎች በአካባቢያችሁ የምታቅዋቸውን በጎ አድራጊ ሰዎች ወላጆቻችሁንና ጎረቤቶቻችሁን በመጠየቅ ግለጹ፡፡ በተጨማሪም ስለማንነታቸው አጭር መግለጫ ጻፉ፡፡

አንዳንድ በጎ ሰዎች ለህይወታችው አስጊ ቢሆንም ሌሎች ሰዎችን ለመርዳት ይጥራሉ፡፡ የሚከተለውም ትረካ ይህንን ያሳያል፡፡

### ለጓደኝነት ዋጋ መክፈል

ከእለታት አንድ ቀን በአንድ የንጉስ ግዛት ውስጥ የሚኖር ሰው በጨካኙ ንጉስ ላይ ተቃውሞ አነሳ፡፡ ንጉሱም በጣም ይበሳጭና ወታደሮቹ ይህን ግለሰብ ይዘው እንዲያመጡና እንዲሰቅሉት ትእዛዝ ይሰጣል፡፡ አመጸኛው ሰው ክሱን ይቀበላል፡፡ ነገር ግን ንጉሱን ባለቤቱንና አምስት ልጆቹን ለመጨረሻ ጊዜ እንዲጎበኛቸው ይጠይቀዋል፡፡ ንጉሱም ተቃዋሚው ሰው ስለመመለሱ ዋስትና ስለሌለው ጥያቄውን አልተቀበለም ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ከተሰበሰበው ሰው መሀል ወደፊት ይመጣና፤ ‘ንጉስ ሆይ አባክህን እኔን በሰውዬው ቦታ እንደዋስትና ተካኝ፤ እሱ ካልተመለሰ ልትሰቅለኝም ትችላለህ’ ይለዋል፡፡ ንጉሱም አንድ ሰው ሌላውን ሰው በመተካት የራሱን ህይወት ለመስጠት መወሰኑ ይገርመውና ተቃዋሚውን ሰው ወደ ቤቱ እንዲሄድና በሶስት ሰአት ውስጥ እንዲመለስ ይፈቅድለታል፡፡

አመጸኛውም ቤተሰቡን ከጎበኘ በኋላ ወደንጉሱ ተመልሶ ይሄዳል፡፡ በመንገድ ላይ ግን ከፈረስ ላይ ይወድቅና በጣም ይጎዳል፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ንጉሱ መድረስ ከነበረበት አንድ ሰአት ያዘገየዋል፡፡ ይሁንና ወደንጉሱ ሲደርስ ዋስትና የገባለት ሰው ሊሰቀል ሲዘጋጅ ይደርሳል፡፡ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮህ ንጉሱን እንደተመለሰና ንፁሁን ሰው እንዲለቀው ይማጸናል፡፡

ንጉሱም ተስማማ ይሁንና ግለሰቡ እሱ የአምስት ልጆች አባትና እነሱን አይቶ ሲመለስ የተጎዳ ግለሰብ ስለሆነ እና እሱ ያላገባ በመሆኑ በሱ ቦታ እንዲተካውና እንዲሰቀል ንጉሱን ይለምነዋል፡፡ንጉሱም በዚህ ከራስ በላይ የሆነ ጓደኝነት በመደነቅ ሁለቱንም ይለቃቸዋል፡፡

ተግባር 4፡- ከላይ በተሰጠው አጭር ትረካ መሰረት ያገኛችሁትን ግብረገባዊ ትምህርት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ መልሳችሁን ለክፍል ተማሪዎች አሳውቁ፡፡

## 5.4. ግለኝነትና የጋራ ጥቅም

ግለኝነት ማለት ለራስ ጥቅም፣ ብልፅግና እና ደህንነት ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው፡፡ ይህ እራስን ማእከል ያደረገና ለሌላው ብልፅግናና ደህንነት ግምት ያለመስጠት ነው፡፡ እውነት ለመናገር ለራስ ቅድሚያ መስጠት ተፈጥሯዊ ሀቅ ነው፡፡ ስለራሳችን ህይወት፣ ጤና እና አስፈላጊ ነገሮች ለኛም ለወላጆቻችንም ማሰብ ይኖርብናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ግለሰባዊ የመማር፣ የመጠበቅ፣ ደህንነትና ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ከበጎነት ጋር ሲነጻጸር ግለሰባዊነት የሚባለው ቃል አሉታዊ ሀሳብን ያመለክታል፡፡ ስግብግብነት ከበጎ ሰው አቋም ጋር ተቃራኒ የሆነ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ ታማኝነትን፣ ትብብርን እና ሀቀኝነትን ይጎዳል፡፡ ይህ ባህሪ ግለሰቡ ራሱንም ለጉደት ይዳርጋል፡፡ ለምሳሌ "ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል" የሚለው አባባል ከላይ የተገለጸውን ሀቅ ያስረዳል፡፡

ስለዚህ እንደ አንድ ጥሩ ዜጋ ስግብግብነትን፣ እራስወዳድነትን እና የሌላ ሰው ፍላጎትን ማጣጣልን አስወግዱ፡፡ ይልቅ ሌላውን ሰው የመርዳት ፍላጎትን ያለንን ማካፈልን፣ ወገንተኝነትንና ትብብርን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡

## 5.5.የጋራ ጥቅም ዋና ዋና ክፍሎች

በዚህ ንዑስ የትምህርት ክፍል ሶስት የጋራ ዋና ዋና ነገሮችን ትማራላችሁ፡፡ እነዚህም የህዝብ ደህንነት፣ የህዝብን ሀብት በአግባቡ መጠቀምና አካባቢን መጠበቅ ወይም መንከባከብ ናቸው፡፡

### 5.5.1. የህዝብ ደህንነት

የህዝብ ደህንነት ማለት ሰላማዊ፤ የተረጋጋ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ ማለት ነው፡፡ የህዝብን ብልጽግና መጠበቅ ወይም መንከባከብ ማለት ህዝብን ከወንጀል፣ ከጥፋትና ከአደጋ መጠበቅ ማለት ነው፡፡

✓ ለምሳሌ እንደ ተማሪ በትምህርታችሁ ውጤታማ እንድትሆኑ ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የትምህርት ቤት ደህንነት ማለት ከአደጋ ነጻ የሆነ በቂ መማሪያ ክፍሎች፣ መጫወቻ ቦታ፣ ንጹህ ውሀና መጸዳጃ ቤትን ያጠቃልላል፡፡ ትምህርት ቤቶችን ከስርቆት፣ ካካላዊ ጥቃት እንዲሁም ከረብሻ የሚጠብቅ ደንብና፣ መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡ ከላይ የተገለጹት አስቻይ ሁኔታዎች አለመኖር ህይወትን ለአደጋ ያጋልጣል፡፡ በዚህም እንደ ተማሪ የራስን፣ የህዝብን እንዲሁም የሌሎችን ደህንነት የሚጠብቁ ደንብና መመሪዎችን ማክበር ይገባችኋል፡፡

### 5.5.2. የህዝብን ሀብት በአግባቡ መጠቀም

የህዝብ ሀብት ማለት ለሰው ልጆች ደህንነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ተፈጥሯዊ፣ ሰው ሰራሽ ቁሶች፣ አገልግሎቶችና ሌሎች ነገሮችን የሚያጠቃልል ማለት ነው፡፡ የህዝብን ሀብት በአግባቡ መጠቀም ማለት ሀብትን በጠንቃቄ፣ በሀላፊነት ስሜት፣ ስነምግባራዊ በሆነ አያያዝና ጥበቃ በአግባቡ መጠቀም ማለት ነው፡፡

ይህ የሆነበት የህዝብን ሀብት በአግባቡ መጠቀም እነዚህን ሀብቶች ከውድመት፣ ከጥፋት ወይም ጉዳት እና ስርቆት ይከላከላል። እነዚህን ሀብቶች ተጠቃሚ እንደ መሆናችን በትብብርና በታላቅነት ስሜት መጠበቅና መጠቀም አለብን። የሚከተለው አጭር ትረካ ጥሩ ተሞክሮ ይሰጣል።



ምስል 5.8 የንብ ቀፎ፣ በትልቅ ዛፍ ላይ ያረፉ ወፎችና በዛፉ ጥላ ስር የተቀመጡ ሶስት መንገደኞች

**የተደረገልህን ውለታ አትርሳ**

ወቅቱ በጋ ነበር። ጸሀይዋ በጣም ትሞቅ ነበር። ሁለት መንገደኞች ምንም መጠለያ ዛፍ በሌለው አቧራማ መንገድ ይጓዙ ነበር። ከምታቃጥለው ፀሐይ መከለያ እየፈለጉ ሳለ አንድ ትልልቅ ቅጠሎችና ብዙ ቅርንጫፎች ያሉት ትልቅ ዛፍ ተመለከቱ። የያዙትን ጓዝ መሬት ላይ ካስቀመጡ በኋላ በዛፉ ጥላ ስር አረፍ አሉ። ትንሽ እረፍት ከወሰዱ በኋላ ከሁለቱ ተጓዦች አንደኛው ሰው ለሌላኛው  ምንም ፍሬ የሌለው የማይጠቅም ዛፍ ነው ይለዋል።

በዚህ መሀል ዛፉ ተበሳጭቶና ድምጹን ከፍ አድርጎ እናንተ ምስጋና ቢሶች በሌላ በኩል ከሚያቃጥለው ፀሐይ በኔ ጥላ ተከላከላችኋል ይሁንና ምንም የማይጠቅም አላችሁኝ ስለዚህ አሁን፤ በአስቸኳይ ከዚህ ተነሱና አከባቢውን ለቃችሁ ሂዱ አላቸው። በዚህ መሀከል አንደኛው ከዛፉ ቅርንጫፍ ላይ የተሰቀለ የንብ ቀፎ መኖሩን አይቶ ለጓደኛው ለካ ዛፉ ተጨማሪ አገልግሎት ይሰጥ ነበር ይለዋል። በስተመጨረሻም ሁለቱም ተጓዦች በሰሩት ስህተት አዝነው ዛፉን ይቅርታ ጠይቀው ጉዟቸውን ቀጠሉ።

ተግባር 5፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተወያዩባቸው

1. ከላይ ካለው አጭር ትረካ ምን ተማራችሁ?
2. በናንተ አስተያየት ከላይ በትረካው ከተገለጸው ሌላ የዛፉ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

## 5.5.3. አካባቢን መንከባከብ

አካባቢን መጠበቅ ወይም መንከባከብ ማለት ጤናማ፣ ዘላቂነት ያለው ለሰው ልጆች ደህንነትና ጥቅም ከሚያስተጓጉሉ ነገሮችና ሊከሰት ከሚችል አደጋ መጠበቅ ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም አካባቢን መጠበቅና ጉዳት ሲያጋጥም ሌላ መተካት ማለት ነው፡፡



መስል 5.9 ተማሪዎች የዛፍ ችግኝ ሲተክሉ



ምስል 5.10 ሰዎች የእርከን ስራ ሲሰሩ

ተግባር 6፡- ጥንድ ጥንድ በመሆን ከላይ የተሰጡት ተግባራት እንዴት አካባቢን ለመጠበቅ እንደሚረዱ ተወያዩ።

## 5.6.የጋራ ጥቅም እንቅፋቶች

የጋራ ጥቅምን በአግባቡ ጥቅም እንዳይሰጥና ቀጣይነት እንዳይኖረው የሚያደርጉ ብዙ እንቅፋቶች አሉ። በጣም ከሁሉም የከፋው የጋራ ጥቅም እንቅፋት ደግሞ ግለኝነት ሲሆን ይህም በራስ ወዳድነት፤ በስግብግብነትና ለሌሎች አለማሰብ ይገለጻል። ሌላው የጋራ ጥቅም እንቅፋት የሆነው የስርቆት ወንጀል ሲሆን ይህም፤ እንደ የኮረንቲ ገመድ ስርቆት፤ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ንብረቶችን ማውደምን ይጨምራል። በተጨማሪም የግል ፍላጎትን ለማህበረሰብ ፍላጎት ሲባል አሳልፎ አለመስጠት የጋራ ተጠቃሚነትን ይጎዳል። ስለዚህ እናንተም ከእንደዚህ አይነት የወንጀል ድርጊቶች ከመቆጠብ በተጨማሪ ሌሎች ድርጊቱን ሲፈፅሙ ካያችሁ በቅድሚያ ለወላጆቻችሁ ቀጥሎም ለትምህርት ቤታችሁ አመራሮች አሳውቁ።

## ምዕራፍ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የጋራ ጥቅም ማለት ለሰው ልጆች፣ ለግለሰቦች፣ ለቡድኖች፣ ለማህበረሰብ፣ ለአገሪቷ ህዝቦችና ለአለም ህዝቦች በሞላ የሚጠቅም ሀብት ማለት ነው።

ይህም ማለት የጋራ ጥቅሞች ሰዎች ፆታን፣ እድሜን፣ ሀይማኖትን፣ ባህልን እና ማህበራዊ ልዩነቶችን አንዱን ከአንዱ ሳይለይ ሁሉም ሰው እንዲጠቀም ማስቻል ማለት ነው። ስለዚህ ሁላችንም ለጋራ ጥቅም የሚውሉ ነገሮችን መጠበቅ አለብን። ይህ ማለት ስለጋራ ጥቅሞች ግንዛቤ ከመስጠት በተጨማሪ ህዝቡም ደህንነታቸውን በማይጎዳ መልኩ በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ፡ ከዚህ በታች የቀረበው ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት ደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

1. ስርቆት የጋራ ጠቅምን የማይጎዳ ድርጊት ነው፡፡

2. የጋራ ጥቅም እንቅፋቶች ሁልጊዜ ሰዎች ሆንብለው የሚፈጥሩት ድርጊት ነው፡፡

3. ዛፎችን መትከለ ለጋራ ጥቅምና ደህንነት ጠቃሚ አስተዋፅኦ አለው፡፡

4. የጋራ ጥቅም ተቋማትን መገንባት የመንግስት ሀላፊነት ብቻ ሳይሆን የህብረተሰቡም ሀላፊነት ነው፡፡

5. ለተቸገሩ ሰዎች የበጎ አድራጎት አገልግሎት መስጠት ያለባቸው ሀብታም ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት፡- ባዶ ቦታዎቹን በትክክለኛ መልሶች ሙሉ፡፡

1. የጋራ ጥቅሞቻችንን ፣ ህይወታችንንና ንብረቶቻችንን ከወንጀል የሚጠብቅ ተቋም ________________ነው፡፡

2. በምዕራፉ በተሰጠው ገለፃ መሰረት አፈርን እንዳይሸረሸር የሚከላከለው ተግባር _________ነው፡፡

3. አለአግባብ የተፈጥሮ ሀብትን መጠቀም ምሳሌ ሊሆን የሚችለው_______________፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## ባህላዊ ቅርሶች

ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምራችሁ ስታጠናቅቁ:-

- ባህላዊ ቅርስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታብራራላችሁ
- የተለያዩ ባህላዊ ቅርሶችን ትለያላችሁ
- ባህላዊ ቅርሶችን የመንከባከብ ጠቀሜታን ዋጋ ትሰጣላችሁ
- የባህላዊ ቅርሶች መንከባከቢያ መንገዶችን ታሳያላችሁ።

### 6.1.የባህላዊ ቅርስ ምንነት

በዚህ ንዑስ ርእስ ስር ሁለት ጠቃሚ ሀሳቦችን ማለትም ባህል እና ቅርስ ምን ማለት እንደሆኑ ትማራላችሁ። ባህል የሚለው ቃል ብዙ ሀሳቦችን ማለትም እውቀትን፣ እምነትን፣ ስነጥበብን፣ ግብረገብነትን፣ ደንብ፣ ልምድና የመሳሰሉትን ይወክላል። በተጨማሪም ሌሎች በሰው ልጆች እንደ ማህበረሰብ አባልነት ተቀባይነት ያገኙ ችሎታዎችንና ልምዶችን ያካትታል። ይሁን እንጂ ባህል የግለሰብ ሳይሆን በተቃራኒው አንድ የተወሰነ በአንድ ላይ የሚኖር ቡድን/ ህዝብ የአኗኗር መንገድና የጋራ ባህሪ ነው።

ባህል በተለያየ ሰው ቁሳዊና መንፈሳዊ ውጤት ይገለጻል ። እነዚህ ሁሉ የሰውን እውቀት፣ እምነት፣ እሴት ፣ ልምድ፣ ባህሪና ክህሎት ይገልጻል። በርግጥ የሁሉም ሰው /ቡድን የተለያየ የአኗኗር ዘዴ፣ ስልጣኔና እምነት አላቸው። ያም እንደገና የአኗኗር ልዩነት እንዳለ ያመለክታል።

ተግባር 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩባቸው፡፡

ሀ. በሰፈራችሁ ሚኖሩ ሰዎች በሀይማኖታዊ በአል ቀናት ምን ያደርጋሉ?

ለ. በሀይማኖታዊ በአል ቀናት ምን አይነት ምግብ ይመገባሉ? ምን ይጠጣሉ? ምን ይለብሳሉ?

ሐ. በሀይማኖታዊ በአል ቀናት እንዴት እራሳቸውን ያዝናናሉ?

እንዲሁም ባህል ከዚህ በታች እንደተመለከተው መሬት የማራስና የማምረት ዘዴያችንም ያሳያል፡፡



ምስል 6.1 የእርሻ መሬት በበሬዎች ሲታረስ



ምስል 6.2 የእርሻ መሬት በእርሻ መኪና ሲታረስ

ተግባር 2፡- ከላይ የተሰጡ ስዕሎች ምንን ያሳያሉ? በመልሳችሁ ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩባቸው

ሀ. የምን ባህልን ያሳያሉ?

ለ. በመካከላቸው አንድነትና ልዩነት አለ?

ቅርስ ሁለተኛው የዚህ ንዑስ ርዕስ ዋና ሀሳብ ነው፡፡ ቅርስ የተቀናጀ የሰብአዊነት ፍጥረት ውጤትና ከአንድ ትውልድ ወደሌላው የተላለፈ ነው ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ስለዚህ ባህላዊ ቅርስ የቀደመውን ሰው ከአሁኑና ከወደፊቱ ጋር ያስተሳስራል፡፡ ስለሆነም ባህላዊ ቅርስ የሰዎች መቼም የማይለወጥ እሴት ፣ እምነት ፣እውቀት ከህሎትና ልምድ ከቀደመው ትውልድ ዛሬ የደረሰውን ያንጸባርቃል፡፡ ስለዚህ ቅርስ የሰዎች የጥንት የስራ ልምድ ግምጃ ቤት ነው፡፡

## 6.2.የባህላዊ ቅርስ አይነቶች

እንደየ ተሰሩበት ገጽታቸው ወይም ቅርጽና አላማ ባህላዊ ቅርሶች በሁለት ዋናዋና ክፍሎች ይመደባሉ፡፡ እነሱም ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶችና ኢ-ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች ናቸው፡፡ ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች የሚባሉት ቁሶቹ በአካል የሚታዩ ሲሆን ነው፡፡ በአይናችን ልናያቸውና በእጃችን ልንዳስሳቸው እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው የሰው ልጅ የፈጠራ ውጤት ናቸው፡፡ ጥቂቶቹ የኢትዮጵያ ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች በብሔራዊ ሎተሪ፣ በቴምብርና በብር ኖት ላይ ይተዋወቃሉ፡፡ለምሳሌ ከዚህ በታች ያለው ሥዕል አዲሱን እ.አ.አ የ2020 የኢትዮጵያ የ100 ብር ኖት ሶስት ተጨባጭ የኢትዮጵያን ባህላዊ ቅርሶች ፎቶ ይዟል፡፡ እነሱም የአክሱም ሀውልት እና የፋሲልን ግንብ በፊት ገጹና ታሪካዊውን ሀረርን የከበባትን የሀረር ግንብ (በተለምዶ ጀጎል ግንብ) ተብሎ የሚጠራውን በጀርባ በኩል ይዟል፡፡





ምስል 6.3 በፊት ለፊት እና ከጀርባ የሚያሳይ የኢትዮጵያ 100 ብር ኖት

ተግባር 3፡- ከዚህ በታች በተገለፁት ሥዕሎች መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩባቸው።

ሀ. ሶስቱ ባህላዊ ቅርሶች ምንን ያሳያሉ?

ለ. እነዚህ ባህላዊ ቅርሶች ለምን የተሰሩ ይመስላችኋል?

በተጨማሪም ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች ከፍልፍል ድንጋይ የተሰሩትን የላሊበላ ቤተክስቲያናትን የካትታል።



ምስል 6.4 የላሊበላው ቤተጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን



ምስል 6.5 ጥንታዊው የሀረር ጀጎል ግንብ

የሀረር ጀጎል ግንብ ታሪካዊ ከተማን ያጎላል፡፡

በረድፍ ተቀርፀው የሚገኙት የጥያ ትክል ድንጋዮች የአከባቢውን ተዋጊዎች በተምሳሌትነት ይወክላሉ፡፡



ምስል 6.6 ጢያ ትክል ድንጋይ

የኮንሶ ባህላዊ መልክአምድርና በረጃጅም ደረቅ ድንጋይ እርከን የተሰሩ በህላዊ መንደሮች፡፡



ምስል 6.7 የኮንሶ ባህላዊ መልክአምድር

በሌላ በኩል ደግሞ ኢ-ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች የሰዎችን የድሮ/ የጥንት በአይን የማይታዩ የጋራ ትዝታዎች ያመለክታል/ ይገልጻል፡፡ እነዚህም ቋንቋን፣ ልምድን ግብረገባዊ ታሪክ፣ ባህል፣ ሙዚቃ፣ ጭፈራ፣ ግጥም ፣ የሀይማኖታዊ በአል አከባበርና አገር በቀል እውቀት እና ግንዛቤ ናቸው፡፡ እነሱም የኑሮ ሁኔታ፣ እምነት፣ መንፈሳዊ የበአል ስርአት እና ማህበራዊ ስነስርአት መገለጫዎች ናቸው፡፡

ከቅድመ አያቶቻችን የወረስናቸው ማህብራዊ እሴቶች፤

- ታላላቆችን ማክበር
- እንግዳ ተቀባይነት
- አርበኝነት
- ለጋስነት ለምሳሌ ደሆችን መርዳት
- በሀይማኖትና በጎሳ ልዩነቶች መቻቻል

ሀይማኖታዊ ባህላዊ ቅርሶች እንደ ጥምቀት እና ኢድአል አድሃ (አረፋ) የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ፍቼ ጨምበላላ፣ የሲዳማ የዘመን መለወጫ በአል እና በትግራይ እና በአማራ ክልሎች የሚከናወኑት የአሸንዳና ሻደይ በኣላት ባህላዊ ቅርሶች ይባላሉ፡፡



ምስል 6.8 የኢድአል አድሃ (አረፋ) እና የጥምቀት በአል አከባበር



ምስል 6.9 የፍቼ ጨምበላላ በኣል አከባበር



ምስል 6.10 የአሸንዳ በኣል አከባበር



ምስል 6.11 የሻደይ በዓል አከባበር

## 6.3.የባህላዊ ቅርሶች የመጠበቂያ መንገዶች

መጠበቅ የሚለው ቃል አንድን ነገር በመጠን፣ በቅርፅ፣ በቀለም፣ በጥራትና በትርጉም እንደ ነበረ ማቆየት ነው። ባህላዊ ቅርሶችን መጠበቅ ቅድሚያ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ነው። ቅርሶቹ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉበትን መንገድ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ተግባር 5፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩና መልሳችሁን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ፡፡

1. ባህላዊ ቅርሶችን ለምን እንጠብቃለን?
2. የባህላዊ ቅርሶቹ መበላሸት፣ መውደም ወይንም ሙሉ በሙሉ መጥፋት ሊያስከትሉ የሚችሉ ምክንያቶችን ዘርዝሩ?

ባህላዊ ቅርሶችን ለጉዳትና ሙሉ በሙሉ እንዲጠፉ የሚያደርጉ በርካታ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም ሰው ሰራሽ ፈተናዎች ለምሳሌ የውጭ ወረራ፣ በአንድ አካባቢ እምነትን፣ ጎሳንና ፖለቲካን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች፣ ሌብነት፣ ዘረፋና ህገወጥ የቅርሶች ዝውውር፣ በእውቀትና ክህሎት ማነስ፣ የገንዘብ እጥረትና ለቅርሶቹ በቂ ጥበቃና ትኩረት አለመስጠት ናቸው፡፡ በተጨማሪም የተፈጥሮ አደጋዎች እንደ ጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ከባድ ዝናብና የመሳሰሉት ቅርሶቹን ሊጎዱ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ ባህላዊ ቅርሶች ተገቢውን ትኩረት ተሰጥቷቸው ከጥፋት ሊጠበቁ ይገባል፡፡ ባህላዊ ቅርሶችን የምንጠብቅባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- በሰዎች ዘንድ ስለቅርሶቹ ምንነትና አይነት፣ ስለሚሰጡት ጥቅም፣ ሊደርስባቸው የሚችሉ ጉዳቶችና የመንከባከቢያ ዘዴዎችን ግንዛቤ መፍጠር፡፡
- ስለ ቅርሶቹ አጠቃላይ ዝርዝር መረጃ ማዘጋጀት ለምሳሌ የተሰራበትን ቀን፣ ለማዘጋጀት የተጠቀሙትን ቁስ፣ የሰራውን ሰው እና የተሰራበትን አላማ መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡
- ቅርሶቹ እንዳይሰረቁና እንዳይወድሙ በሰዎች የሚደረገውን ጥበቃና ትብብር ማጠናከር፡፡
- ደህንነቱ የተጠበቀ ቤተ-መዘክር መገንባት፡፡
- ቅርሶቹን ለመጠበቅና ለመንከባከብ ጠንከር ያለ ህግ ማውጣትና ተፈፃሚነቱን መከታተል፡፡
- ጉዳት የደረሰባቸውን ቅርሶች መጠገን ናቸው፡፡

## 6.4.የባህላዊ ቅርሶች አስፈላጊነት

የማነቃቂያ ጥያቄ፡- ባህላዊ ቅርሶች አስፈላጊነት ምንድን ነው?

ባህላዊ ቅርሶች ኢትዮጵያዊ ማንነትንና በአለም አቀፍ ደረጃ በተጨባጭ የታሪክ፣ የስልጣኔ እንዲሁም የሰው ልጅ መገኛ መሆናችንን የአለም አቀፍ ማህበረሰብ ግንዛቤ እንዲኖረው በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ:: የቀደምት እውቀቶቻችን ማንነታችንን፣ የጋራ ተጠቃሚነታችንን ፣ አንድነትና ልዩነታችንን፣ እንዲሁም ስኬትና ድክመታችንን ያሳያሉ:: ይህን በማድረግም ብሄራዊ አርማችንን አንድነታችንንና ጥምረታችንን እንድናውቅ ይረዱናል:: አንድነት ለፖለቲካ መረጋጋትና ቀጠይነት ያለው ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ለመገንባት የማእዘን ድንጋይ ነው፡



ምስል 6.12 የኢትዮጵያውያንን አንድነት የሚያሳይ ታሪካዊው የአደዋ ጦርነት

ከዚህ በተጨማሪም ማንነታችንንና ልዩ ባህሪያችንን በማጉላት የአካባቢ ሰዎችን ውጤታማነት መረጃ በመስጠት ባህላዊ ቅርሶች በጎ የሆነ በባህሎች መካከል ውይይትን እውቀትንና ክህሎት መጋራትን ያሳድጋሉ:: እነዚህ የባህል ቅርሶች በተለያዩ ባህሎች መካከል መከባበርን ይፈጥራሉ:: ባህላዊ ቅርሶች ለሀገር ምጣኔያዊ ሀብት እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ::

ለምሳሌ ከውጪ ጎብኚዎች በሚገኘው የውጪ ምንዛሪ ለማግኘት፣ ለመጓጓዣ፣ ለመንገድ እና ለማህበራዊ አገልግሎቶች እድገት እንዲሁም ለተለያዩ ሰራተኞች የስራ እድል ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ የእደጥበብ ውጤቶች አልባሳት እና ሌሎች እቃዎችን ለውጪ ጎብኚዎች በመሸጥ ለዜጎች የንግድ አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡



ምስል 6.13 የውጪ ጎብኚዎች ብሄራዊ ቤተ-መዘክርን ሲጎበኙ

ጎብኚዎች ባህላዊ ቅርሶቻችንንና ታሪካዊ ቦታዎቻችን በመጎብኘት የገዟቸውን ባህላዊ ቁሳቁሶች በመጠቀምና የጎበኟቸውን ታሪካዊ ቦታዎች በማስረዳት ወደመጡበት አገር ሲመለሱ ለአለማቀፉ ማህበረሰብ የኢትዮጵን በጎ ገፅታ ያስተዋውቃሉ፡፡ ይህ ደግሞ ሌሎች ጎብኚዎች መዋለንዋያቸውን ይዘው በተለያየ መስክ በመሰማራት ወደ ሀገራችን እንዲመጡ የሚያደርግ ሲሆን የአገር ውስጥ ጎበኚዎችንም ያበረታታል፡፡

## ምዕራፍ ማጠቃለያ

ባህላዊ ቅርሶች ማለት ቀደም ሲል የነበረውን (የቀድሞውን) እውቀት፣ እምነት፣ ልማድ፣ የህይወት ዘይቤ፣ እሴትና ወዘተ የሚያመለክት ነው። ባህለዊ ቅርሶችም አሁናዊና የወደፊት ጊዜን ያቆራኛሉ።ይህንን በማድረግ ባህላዊ ቅርሶች የሰው ልጆችን ቀደምት ልምድ ማከማቻ ናቸው ማለት ይቻላል። በገጽታቸው፣ በቅርጻቸው ወይም እንደ ተሰሩበት አላማ ባህላዊ ቅርሶች በሁለት ይከፈላሉ። እነዚህም

1. ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶችና
2. ኢ-ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች ናቸው።

ባህላዊ ቅርሶች ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ አላቸው። ነገር ግን በሙሉም ይሁን በከፊል በሰዎችና በተፈጥሮ አደጋ እንዳይጎዱ በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ አለብን።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ በ(ሀ) ረድፍ የተዘረዘሩትን በ(ለ) ረድፍ ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ

| /ሀ/ | /ለ/ |
| --- | --- |
| 1. የሰዎች የኑሮ ዘይቤ | ሀ. የጦር መሳሪያ |
| 2. ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያመነጩ | ለ. ሀይማኖታዊ በአል |
| 3. ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች | ሐ. ቱሪዝም |
| 4. ቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች ያልሆነ | መ. ባህል |
| 5. ታላላቆችን ማክበር | ሠ. የኢትዮጵያ ባህላዊ እሴት |

ክፍል ሁለት፡ዐረፍተ ነገሩን አንብባችሁ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሳችሁን ፃፉ::

1. የሌላውን ባህል ማክበር ተቻችሎ በሰላም ለመኖር አስተዋጽኦ ያደረጋል::
2. ባህላዊ ቅርሶች የመዝናኛ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ::
3. ባህላዊ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግስትና የሁሉም ዜጋ ሀላፊነት ነው::
4. ባህላዊ ቅርሶች የሚጎዱት በሰው ልጆች ተግባር ብቻ ነው::
5. የኢትዮጵያ ሰነደ ቃላማ የኛ ባህላዊ ቅርሳችን ነው::